# ቤተክርስቲያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት

## የሚመሩ መሪዎች
## የህይወት ቡድን መሪ ማሰልጠኛ

Dynamic Churches International
ዳይናሚክ ቸርችስ ኢንተርናሽናል

Dynamic Churches
International

# ቤተክርስቲያንን በኃይል ወደሚንቀሳቀስ ሕይወት መምራት

## የሚመሩ መሪዎች
## የሕይወት ቡድን መሪ ማሰልጠኛ

*Dynamic Churches International*
**International/Canadian Address:**
164 Stonegate Close,
Airdrie, Alberta, Canada, T4B 2V2
(403) 912-4438
dcimiddleton@shaw.ca
www.dynamicchurches.org

እዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምንባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው።

Copyright © 2009 Dynamic Churches International.
All rights reserved including translation.
ከዚህ መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል መግለበጥም ሆነ ማባዛት ያለ ጽሑፍ ፍቃድ የተከለከለ ነው። ይሁንና ከዚህ መጽሐፍ በግል ለመጠቀም ቅፆችን መገልበጥ ይቻላል።

# ማውጫ


**ይህንን የስልጠና መፅሀፍ ለመጠቀም የሚያስችል ግንዛቤ**

ገፅ

**መግቢያ** 1

**ክፍል አንድ የመቆጣጠሪያ ቅፅ** 3

- የቤተክርስቲያን የመመስረቷ ዓላማ 5
- የሥራ ሐላፊነቶች 6

**ክፍል ሁለት የመቆጣጠሪያ ቅፅ** 9

- የወደፊትህን ህይወት በር መክፈት 11

**ክፍል ሦስት የመቆጣጠሪያ ቅፅ** 15

- የመሪው ኃላፊነት 17
- የውጤታማ ሰዎች የአፈፃፀም ሂደት 18

**ክፍል አራት የመቆጣጠሪያ ቅፅ** 23

- ደቀመዝሙር ለማድረግ መንፈሳዊ ዝግጅት 25
- የሚያድግ መንፈሳዊ ቤተሰብ 27
- ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት 28
- ወደ ብስለት ማደግ ሂደት ነው፡፡ 30

**ክፍል አምስት የመቆጣጠሪያ ቅፅ** 31

- የህይወት ታሪክ ወርክሾኘ 33
- የአንድነት ጊዜ መመሪያዎች 37

**ክፍል ስድስት የመቆጣጠሪያ ቅፅ** 43

- የመሪነት መሠረት 45
- በግንኙነት ውስጥ ያለ አዲስ አንድነት 46
- እንዴት የቡድን ተሳትፎ ማዳበር ይቻላል? 48
- የአገልግሎት ኃላፊነት ሰሌዳ 50

**የምስክር ወረቀት** 51

# የሚመሩ መሪዎች
# የዚህ መፅሐፍ አጠቃቀም

እነዚህ የስልጠና ክፍለ ጊዜዎች በተሳካ ሁኔታ የህይወት ቡድንህን ለመምራት፣ የእያንዳንዱ የቡድን አባል አሰለጣጠን ለማቀናጀትና ተተኪ መሪህን የራስዋን/ሱን ቡድን እንድትመራ/ዲመራ ለማዘጋጀት ያስታጥቅሃል።

እያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ አሰልጣኙ የራሱን የህይወት ቡድን መሪዎች ለማሰልጠን የሚጠቀምበት ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

> **ማስታወሻ፡-** እያንዳንዱ የቡድን መሪ ይህንን ስልጠና ከመጀመሩ በፊት በተተኪ መሪነት የሰለጠነና የተተኪ መሪ ስልጠናን ያጠናቀቀ መሆን አለበት።

**የህይወት ቡድኑ መሪ ተግባራት**

- ከአሰልጣኙና ሌሎች የቡድን መሪዎችን ከማግኘቱ በፊት እያንዳንዱን ክፍል በማጥናት መዘጋጀት ይኖርበታል። (ብዙውን ጊዜ በወር ለአንድ ሰዓት ለሆነ ግንኙነት)
- በዚህ ጊዜ በአንድነት በመሆን በግንዛቤያቸው እርግጠኛ ለመሆን በመልዕክቱ ዋና ሐሳብ ላይ ውይይትና ክለሳ ያደርጋሉ።
- ብዙዎቹ እነዚህ መርህዎች በግል ህይወትህ ወይም በቡድንህ ውስጥ ተግባራዊ የሚሆኑ ናቸው። አንዳንዶቹ ቡድኑ የሚመራቸው ናቸው። ይህንን መፅሀፍ ቅዱሳዊ ዕውነት ለማስተማር በቡድኑ ውስጥ ጊዜ መመደብ ይኖርብሃል ወይም የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜውን መጠቀም ይኖርብሃል።

ይህ መጽሐፍ ***ቤተክርስትያንን በኃይል ወደ ተሞላ ሕይወት መምራት*** በተሰኘ ርዕስ ከሚሰጡ በርካታ ትምህርቶች አንዱ ነው። **የሕይወት ቡድኑ መሪ ስልጠና** ከአጠቃላይ ሰዎችን ለሚፈለገው አላማ ለማስራት ከተያዘው ስልት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ የሚከተለው ነጥብ ያሳያል።

| **የስልጠና መፅሀፍ** | **ስልጠናው የሚሰጠው ሰው** |
|---|---|
| 1. የፈጣን ዕድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ስልጠናና ወርክሾፕ | - ለመጋቢያንና ለመሪዎች አንድ ለአንድ ደቀመዝሙር የማፍራት እና ትንንሽ ቡድኖችን ለማብዛት<br>- ከላይ የተጠቀሱትን ወደ ህይወት ቡድንነት ለማቀናጀት<br>- አገልጋዮችን ለማሳደግና የህይወት ቡድኑን በማስፋፋት ቤተክርስትያንን ደቀመዝሙር የምታፈራ ለማድረግ |
| 2. መምራትን መማር<br>- የተተኪ መሪ ስልጠና | - የህይወት ቡድን መሪዎች ተተኪዎቻቸውን ሲያሰለጥኑ የሚጠቀሙበት |
| 3. የሚመሩ መሪዎች<br>- የህይወት ቡድን መሪ ማሰልጠኛ | - አሰልጣኞች የህይወት ቡድን መሪዎቻቸውን ሲያሰለጥኑ የሚጠቀሙበት |
| 4. የአሸናፊዎች ቡድን<br>- የአሰልጣኞች ማሳደጊያና ማስተማሪያ | |
| 5. አልፎ መድረስ<br>- ቤተክርስትያን ለቤትክርስትያን መከታተል | - መጋቢያን አሰልጣኞቻቸውን ለማሳደግ የሚጠቀሙበት<br>- በክልል ወይም በአለምአቀፍ ደረጃ መጋቢያንና መሪዎች ሌሎች ቤተክርስትያናትንለማገዝ የሚጠቀሙበት |

**እነዚህ ሁሉ መጽሐፍት በቢሮአችን ወይም ከታች በተቀመጠው መረጃ መረባችን በኩል ይገኛሉ።**

# አጠቃላይ ሰዎችን የማሳደጊያ ስልት

| ዓላማ | የህይወት ቡድን | መሪና ለማጅ | አሰልጣኝና መሪ | መጋቢና መሪዎች | ቤ/ክ ለቤ/ክ ክትትል |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. አቀባበል ፍቅር/ማካፈል | እርስ በእርስ መተዋወቅ | ወንድማማችነትን/ ጓደኝነትን ማጎልበት | ለቤተክርስቲያንና ለህብረተሰቡ ያለውን ሸክም ማካፈል | ሰዎችን ለመድረስ ለሚደረገው አገልግሎት ራዕይንና ጥልቅ ስሜትን መፍጠር | - መጋቢያንን ሁሉ መተዋወቅ<br>- ለአንድነታችንን ዋጋ መስጠት<br>- እርሰ በእርስ መገላገልና ቤ/ክ ከቤ/ን ጋር |
| 2. አምልኮ መዝሙር፣ መፀለይና ማመስገን | እግዚአብሔርን ማምለክ ለእርስ በእርስና ደህንነትን ላላገኙ ጓደኞች መፀለይ | እግዚአብሔርን ማምለክና ለእርስ በእርስ፣ ለቡድኑ አባላት፣ ለወንጌል ስርጭትና ለእድገት መፀለይ | እግዚአብሔርን ማምለክና ስለተተኪ መሪው፣ ስለ ቡድኑ አባላትና ስለተወለዱ አዳዲስ ቡድኖች ማመስገን | እግዚአብሔርን ማምለክና ለመሪዎች ለወደፊት ምሪቱ ማህበረሰቡን ለመድረስ ለቤተክርስቲያን ተከላና ለመስፋፋት መፀለይ። | እግዚአብሔርን ማምለክና እርስ በእርስ አገልግሎቶች ለቤተክርስቲያን አንድ መሆን ለመስፋፋት/ሌሎች ቤ/ክ ለማዘጋጀት ከተማን/አካባቢን ሙሉ በሙሉ ለማውረስ የፀሎት ስልት |
| 3. መማረክ መድረስ | ክርስቶስን ለመመስከር መማር አዳዲስ ሰዎችን ለመድረስ መፀለይ | የህብረቱን አባላት ክርስቲያን ላልሆኑ ጓደኞቻቸው እንዲፀልዩና እንዲደርሷቸው ማዘጋጀትና ማበረታታት | የወንጌል ስርጭት በህብረቱ ልዩ ጊዜዎችና በቤተክርስቲያን ደረጃ ማቀድ | - ለየት ባሉ ጊዜዎች ቤ/ክ አቀፍና ከተማ አቀፍ የወንጌል ስርጭት እቅድ ማውጣት<br>- ባህል ዘለል አገልግሎት<br>- የአጭር ጊዜ የአገልግሎት ኘሮጀክት | - ለአካባቢ ወይም ለከተማ ወንጌል ስርጭት ስልት ዕቅድ ማውጣትና ለተግባራዊነቱ መተባበር<br>- በአንድ ሌላ ከተማ/የዓለም ክፍል መኖር |
| 4. የእግዚአብሔር ቃል መማር/መፅሐፍ ቅዱስ ጥናት «የማሰልጠን ችሎታ» | የክርሰትናን ህይወት የመኖሪያ መንገዶች | ቡድናችንን የማሳደጊያና ማባዢያ መንገዶች | ቡድንህን የምትመራበት መንገድ | - ራዕዩን ማስፋፋት<br>- ታላቁን ተልዕኮ ለመፈፀም መፅሐፍ ቅዱሳዊ ስልት ማዘጋጀት | ለከተማችን፣ ለሃገራችንና ለዓለማችን እግዚአብሔርን ማመን |
| 5. ሥራ ማገልገል/መሪ እድገት አንድ ለአንድ | በኃይል የተሞላ መሰረታዊ<br>በኃይል የተሞላ ደቀመዝሙር ማድረግ | ለመምራት በኃይል የተሞላ ማካፈል | ቡድንህን መምራት | የተረጋገጠለት/የተመሰከረለት ስልጣኝ<br>የእግዚአብሔር ራዕይ መያዝ | - የህይወት በህይወት ክትትል<br>- የእግዚአብሔርን ራዕይ መያዝ<br>- ሌሎች አብያተክርስቲያናትን ማዘጋጀት |
| • ትንሹ ህብረት በአንድነት እንደ ህብረት | የትንሹ ህብረት ጊዜ | በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾኘና ዓመታዊ የፆምና የፀሎት ጊዜ | በፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትና ዓመታዊ የፃምና የፀሎት ጊዜ | - ቡድንኑን መገንባት<br>- ለሱሰኞች አገልግሎት<br>- ዓመታዊ የፆምና የፀሎት ጊዜ | - ከተማችንን፣ ከሃገራችን ባሻገር ለመድረስ ስልት መንደፍ<br>- በከተማ አቀፍ የመዘጋጃ ልዩ ጊዜ መተባበር |

# *የሚመሩ መሪዎች*

## *መግቢያ*

## *የመሪዎች ፍላጎት*

ዛሬ ከፍላጐቶች ሁሉ ትልቁ ፍላጐት የሆነው የመሪዎች ፍላጐት ነው። እነዚህም መሪዎች በመሪነት ስፍራ ብቻ የሚቀመጡ መሪዎች አይደሉም፤ ነገር ግን ***የሚመሩ መሪዎች*** ናቸው። በክርስቶስ ፍቅር የሚነዱና የሚንቀሳቀሱ፣ ለሰዎች ርህራሄና ፍቅር ያላቸው ወንዶችና ሴቶች ያስፈልጉናል። ለእግዚአብሔር ዓላማ መፈፀም ይህም ማለት ማንኛውም ሰው የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ግንዛቤ አግኝቶ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙና እንደ ጌታ ለመቀበልም ሆነ ላለመቀበል ዕድሉን ለመስጠት የቸኮለ ልብ ያላቸውና ግልፅ ራዕይ ያላቸው መሪዎች ያስፈልጉናል።

እንዴት እንደዚህ ያሉ ሰዎችን ልናገኝና ልናሳድግ እንችላለን?

ከፊትለፊታቸው ላለው ፈታኝ ሥራ እንዴት ልናሰለጥናቸውና ልናዘጋጃቸው እንችላለን?

ራስህን እንዲህ ብለህ ልትጠይቅ ትችላለህ፣ ***«እንዴት አድርጌ እነርሱ የሚፈልጉትን ዓይነት መሪ ልሆን እችላለሁ?»***

***መምራት በየደረጃው በተቀመጡ የእግዚአብሔር ህዝቦች ውስጥ ያሉ መንፈሳዊ ስጦታዎችንና የፈጠራ ምንጮችን የማቀናጀት ጥበብ ነው።***

## *የመሪነት ሰልጣኞች ቡድን ለምን አስፈለገ?*

ቤተክርስቲያን ከዚህ በፊት ያደረገቻቸውን ነገሮች ከዛሬው ጠቀሜታቸው አንፃር ተመልሳ የምታይባቸው ወሳኝ የታሪክ ጊዜ ላይ ትገኛለች። ሁልጊዜ ለበለጠ ውጤታማነት ደግሞ ማቀናጀት ያስፈልጋል። ይሄ ደግሞ ብዙ ጥያቄዎችን ቡዙ ግራመጋባቶችን ያስነሳል። ቤተክርስቲያን ወደ ተለየ አዲስ አቅጣጫ እንድትጓዝ ካስፈለገ መሪዎች ከዛሬው የሰዎች ፍላጐት ጋር እንዲስማሙ እንደገና ሊሰለጥኑና ለነገዋ ቤተክርስቲያን ሊዘጋጁ ያስፈልጋቸዋል።

እያንዳንዳችን አንድ ዓይነት ሃሳብ ያለንና ለመማርና ለማደግ የጋራ ፍላጐት ያለን የቡድኑ አካል ልንሆን ያስፈልጋል። እነዚህን በምንወያይበትና ተግባራዊ በምናደርግበት ጊዜ እያንዳንዳችን የተለየ ግንዛቤ እንዳለን እንረዳለን ደግሞም እንጠቀማለን። ሁላችንም እነዚህን ነገሮች በጋራ ስንደርስባቸው ወደ ወሳኝ መርሆች ሙሉ መረዳት እናድጋለን።

አውዱ ለመሪነት የስልጠና ጊዜ ትልቁ ግብዓት ነው። ምሳሌ የሆኑ መርህዎችን እናያለን። ለአዳዲስ አሰተሳሰቦች ያለን ግንዛቤና አድናቆት የተማርናቸውን ትምህርቶች በአገልግሎታችን ውስጥ እንድንለማመዳቸው እንድንፈልግ ያበረታቱናል። ደግሞም እንደ መሪ ልናገለግል ይገባል። የማካፈልና የፀሎት ጊዜዎች በህይወትህ ልዩ የመንከባከቢያ ጊዜን ያረጋግጣሉ።

## የህይወት ለህይወት ክትትል

ከቡድኑ የመገናኛ ጊዜ ውጪ በህይወትህና በአገልግሎትህ ልታሳድጋቸው የምትፈልጋቸውን መርሆች ህይወቱን በመርሆቹ በመራ አንድ ሰው ሥር ክትትል ልታገኝ ትችላለህ። ይህ የአንድ ለአንድ ክትትልና ትንሹ ቡድን ለእድገትህ ምርጥ የማደጊያ አካባቢ ይሰጡሃል።

## የሰልጣኝ ቡድኑ አሰልጣኞች ዓላማ

በክርስቶስ እያደጉ ያሉትንና ሌሎችን ደቀመዝሙር አድራጊ ቡድን በማድረግ ማህበረሰባቸውን በክርስቶሰ ኢየሱስ ወንጌል ለመድረስ የሚያነቃቁና የሚረዱ መሪዎችን መንከባከብና መውደድ ነው።

## የሰልጣኝ ቡድኑ አሰልጣኞች ግብ

- እያንዳንዱን ሰው የመውደድ እና የተቀባይነትን የማግኘት ስሜት እንዲሰማው ማድረግ
- የእያንዳንዱን ሰው አካላዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ለማሟላት
- እያንዳንዱን ሰው ሌሎችን በትንሽ ቡድን ውስጥ ይመራ ዘንድ ማዘጋጀት
- እያንዳንዱን ሰው ሌሎችን በአንድ ለአንድ ደቀመዝሙር ማሰልጠን ይችል ዘንድ ማዘጋጀት
- እያንዳንዱን ሰው ለማጁንና አስተናጋጁን ማሳደግ እንዲችል ማዘጋጀት
- በቂ ደቀመዝሙር አድራጊ ቡድኖች በመምራት ማህበረሰቡን ለክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል እንዲመቻች የሚያደርጉ በቂ የሆኑ መሪዎችን ማሳደግ

## የሚመሩ መሪዎች ስልጠና ቡድን አጀማመር

በቤተክርስቲያንህ ያለች የመጀመሪያዋ ትንሿን ቡድን ምናልባት በመጋቢው ልትመራ ትችላለች። ነገር ግን ለማጁ መሪ የራሱን ቡድን መምራት ሲጀምር፣ የመጋቢውም ሥራ በቀላሉ ከእነርሱ ጋር መገናኘትና በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ በተከሰቱ ጉዳዮችን መረጃ በመለዋወጥ እርስ በእርስ መበረታታት ይሆናል። ብዙ ቡድኖች በለማጀቻቸው መሪ መሆን ሲመሰረቱ፣ የዚያን ጊዜ የሚመሩ መሪዎች ማሰልጠኛ ቡድንኑ በመደበኛ መጀመር ይቻላል።

**ማሳሰቢያ**፦ የስልጠና ቡድኑን የሚመሩ መሪዎች ለማሰልጠን የሚጠቅመውን ስልጠና፤ በርከት ያሉ ትንንሽ ቡድኖች ሲመሰረቱ መጀመር ይገባሃል።

መሪዎቹ እንዲሳተፉ የሚመች ጊዜ መድብ። ምናልባት ተሳትፏቸውን ከሚያደናቅፍ ሌሎች ኃላፊነቶች ነፃ ልታደርጋቸው ያስፈልግሀ ይሆናል። ምክንያቱም ትንንሽ ቡድኖች ወሳኝ ከመሆናቸው አንፃር ይህ ስልጠና ከፍተኛ ቅድሚያ ሊሰጠው ግድ ይሆናል።

# የሚመሩ መሪዎች
## ክፍል አንድ

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው፡፡

**ከመሪዎች ቡድንህ ጋር ከመገናኘትህ በፊት**

☐ 1. ***መግቢያውን*** አንብብ፡፡ ይህ የመሪዎች ቡድን እንዴት በተሳካ ሁኔታ የህይወት ቡድንህን ለመምራት እንደሚረዳህና የወደፊት መሪነትህን እንደሚያሳድገው ለማካፈል ተዘጋጅ፡፡

☐ 2. ***የቤተክርስቲያን ዓላማ ፣ የህይወት ቡድናችን ዓላማና የህይወት ቡድናችን ግብ*** የሚሉትን ክፍሎች አንብብ፡፡ እንዴት ይህ አገልግሎት ህይወትን እንደሚቀይርና እኛንም እንደ ቤተክርስቲያን በማህበረሰባችን ያሉትን ሌሎችን ለመድረስ እንደሚያዘጋጀን እምነትህ ምን እንደሆነ ለማካፈል ተዘጋጅ፡፡

☐ 3. ወደ ***ቡድኑ ይዘት*** እና ***የሥራ ዓይነት*** ወደሚለው ሂድ፡፡ የአንተን የኃላፊነት ቦታ ለይና ለአሰልጣኝ ወይም ለሌሎች መሪዎች ግለፅላቸው፤ ማንኛውን ዓይነት ጥያቄ ጠይቅ፡፡

☐ 4. ***የቡድን መመሪያዎች*** የሚለውን አንብብ፡፡ ከመሪዎች ቡድን ጋር ለመወያየት ተዘጋጅ፡፡

☐ 5. ከዚህ በታች ያለውን ***ሪፖርት*** አጠናቅ፡፡

ከመሪነት ቡድንህ ጋር የሚጠናቀቅ፡፡

☐ 6. እርስ በርሳችሁ ተዋወቁ፡፡ አንዳችሁ ላንዳችሁ እንደሚመለከታችሁ ግለፁ፡፡

☐ 7. ከላይ ከ 1 እስከ 5 ያሉትን ከተወያያችሁባቸው በኋላ መልክት አድርጉባቸው፡፡

**በዚህ ወር የህይወት ቡድንህን ለመምራት ኃይልን ይሰጣችሁ ዘንድ የሚከተሉትን ተወያዩባቸው፡፡**

☐ 8. የመሪ አስፈላጊነት በቤተክርስቲያናችን

☐ 9. የታላቁ ተልዕኮን መፈፀም አስፈላጊነት

☐ 10.የህይወት ቡድን አባላትን ሌሎችን ለመድረስ በሚያበቃ ዕድገትና ቅንአት የማሳደግ አስፈላጊነት፡፡

☐ 11. የራሳችንን የመሪነት ችሎታ የማሳደግ አስፈላጊነት፡፡

**የህይወት ቡድንህ ሪፖረት**

☐ 12. ________ ሰዎች በመደበኛነት ይሳተፋሉ።

☐ 13. ________ አዳዲስ ተሳታፊዎች በዚህ ባሳለፍነው ወር ተካፍለዋል።

ስም____________________________________________________________

አድራሻ__________________________________________________________

_______________________________________________________________

☐ 14. በአንድ ለአንድ ስልጠና ላይ ያሉ

ዳይናሚክ መሰረታዊን ____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል

ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ ________________________________________ን ያሰለጥናል

____________________ ____________________ን ያሰለጥናል

ዳይናሚክ ማካፈልን ____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል

☐ 15. ________ ሰዎች በዚህ ወር በቡድናችን ውስጥ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል።

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 16. ለእርስ በእርስና ለቡድን አባላቶቻችን ፀልይ።

☐ 17. ወደ ክፍል ሁለት የመልመጃ ዝግጅት አልፈህ ሂድ።

☐ 18. ለሚቀጥለው የሚመሩ መሪዎች ለሚለው ክፍለጊዜ ቀን ______________ ሰዓት __________ ቦታ ________________________________ መድብ

# የቤተክርስቲያናችን ዓላማ

የመጨረሻው የቤተክርስቲያናችን ዓላማ የታላቁ ተልዕኮ ነው፡፡ (ማቴ 28÷18-20) መላው ዓለም የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሰምቶ ምላሽ እስኪሰጥ ድረስ ደቀመዛሙርትን የሚያፈሩ ደቀመዛሙርት እንሰራለን፡፡ በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ ደቀመዛሙርት ኢየሱስ እንደኖረው ለመኖር የሚፈልጉና ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው የህይወት እርምጃ በአያሌው የሚደሰቱና በክርስቶስ ኢየሱስ ስላገኙት አዲስ ህይወት ለሌሎች አለመናገር የማይሆንላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ የህይወት ቡድን አገልግሎት እያንዳንዱን የቤተክርስቲያናችንን አባል እንደዛ ያለውን ሰው እንዲመስል ለመገንባት እንዲችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡ በዚህ ስልጠና መሪ ለመሆን እድሉን አግኝተሃል፡፡

# የህይወት ቡድናችን ዓላማ

በፍቅርና በእንክብካቤ ወደ ክርስቶስ የሚያድግ የሚዋደድና የሚተሳሰብ እና የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች የሚያካፍል ቤተሰብ መሆን፡፡

## የህይወት ቡድናችን ግብ

- እያንዳንዱን ሰው መውደድና ተቀባይነትን እንዲሰማው ማድረግ
- የእያንዳንዱን ሰው አካላዊ፣ ስነልቦናዊና መንፈሳዊ ፍላጐት ማሟላት
- በ6 ወር ውስጥ እያንዳንዱ ሰው ከ 6-8 የሚደርሱ ትርጉም ያላቸው ግንኙነቶችን በቡድኑ ውስጥ ካሉ ሌሎች ሰዎች ጋር እንዲያሳድግ
- በሌሎች አገልግሎቶች ውስጥ እንዲገቡ ማደፋፈር፡፡ ለምሳሌ ማህበራዊ ጉዳዮች፣ አምልኮ፣ የሰንበት ትምህርት
- እያንዳንዱ ሰው የራሱን መንፈሳዊ ስጦታ ለይቶ በማወቅ፤ ሌሎችን ለማገልገል እንዲጠቀምበት መርዳት
- እያንዳንዱን ሰው የተጠመቀና የቤተክርስቲያናችን ንቁ ተሳታፊ አባል ማድረግ
- እያንዳንዱን ሰው በዳይናሚክ መሰረታዊ፣ በዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግና በዳይናሚክ ማካፈል ለማሰልጠን
- በ6 ወሩ አንድ አዲስ ቤተሰብን ወደ ቤተክርስቲያን መጨመር
- ለማጅ መሪዎችን ለማሳደግና በየ6 ወሩ አንድ አዲስ የህይወት ቡድን መመሰረት
- ህብረተሰባችንን ለክርስቶስ ለመድረስ እንዲቻለን በቂ የህይወት ቡድኖችን መመስረት

### የቡድኑ ይዘት

ይህ ይዘት በየሳምንቱ ሊለያይ ይችላል፤ ነገር ግን የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል፡፡

**አቀባበል** (15-20 ደቂቃ)

- መክፈቻ ፀሎት
- ማካፈል፣ ምስጋናና ሪፖርት

**አምልኮ** (15-20 ደቂቃ)

- መዝሙር መዘመር ወይም ከመዝሙር መፅሀፍት ማንበብ

**ወንጌል ስርጭት** (20-30 ደቂቃ)

- በተፅዕኖ ክልልህ ላለው ለውጥ ሪፖርት አቅርብ፡፡
- ለወንጌል ስርጭት ስልትና ሁኔታዎችን አቅድ
- በአንድ ለአንድ ስልጠና ውስጥ የተያዙትን ሰዎች ለውጥ ማየት፡፡

**የእግዚአብሔር ቃል** (20-30 ደቂቃ)

- *የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት*
- *ፀሎት*

***መዝጊያ***

- *ማስታወቂያዎችና ፀሎት*
- *መዝናኛዎች /ማነቃቂዎች/*

***ሥራ***

- *ለደቀመዛሙርነትና ለመሪ ግንባታ የአንድ ለአንድ የስልጠና ክፍለጊዜዎች* (*በሳምንቱ ውስጥ*) *እነዚህን መመሪያዎች መከተል ውጤታማ የህይወት ቡድን እንዲኖርህና እራስህን ሌሎችን በማሰልጠን ተመሳሳይ ሥራ እንዲሰሩ ያስችልሃል።*
- *የፈጠራ ሥራ ይኑርህ ግልፅ ሁን የሚያዝናኑ ነገሮችም ይኑርህ አስታውስ ግብህ /ግባችሁ/በፍቅርና በመቀባበል በሆነ ህብረት ውስጥ ህይወታችሁን እርስ በእርሳችሁ መከፋፈል ነው። እየተጠቀምክበት ያለው ነገር የሚተላለፍ  እንደሆነ እርግጠኛ ሁን። ምክንያቱም በቡድንህ ውስጥ የምታደርገው በአዲሱ ቡድን ውስጥ የሚዛመት ይሆናል። በርካታ ሰዎች ባለቤትነትን ይወስዱ ዘንድ፤ የህይወት ቡድንህን የሥራ ኃላፊነቶች ከፋፍለህ አስቀምጥ ። መሪዎችም በልምምድ ውስጥ ያድጋሉ።*

# *የሥራ ምድብ*

## አሰልጣኝ

**ኃላፊነቶቹ**

1. *የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል።*
2. *ለጌታ ሥራ በታማኝነት አስራት ማውጣት።*
3. *የህይወት ቡድን መሪዎች ስልጠናን ማጠናቀቅ።*
4. *ትንንሽ ቡድኖችን መምራት።*
5. *በየ4 ሳምንቱ ከመሪዎችህ ጋር «የሚመሩ መሪዎች - የህይወት ቡድን መሪ ስልጠና» የተሰኘውን ስልጠና ለማጠናቀቅ መገናኘት።* (*በግል ወይም በአንድነት*) *ይህ ጊዜ፡-*
   *ሀ/ የማበረታቻና ራዕይ የመካፈል ጊዜ ይሆናል።*
   *ለ/ ለአምስቱ የህይወት ቡድን ዓላማዎች የተጠያቂነት ጊዜ ይሆናል።*
   *ሐ/ የመከታተያ፣ የመመካከሪያ፣ የመበረታቻና የማፅኛ ጊዜ ይሆናል።*
   *መ/ የፀሎት ጥያቄዎች፣ የቤተክርስቲያን አቀፍ ክስተቶችንና ሌሎች መረጃዎችን መለዋወጫ ጊዜ ይሆናል።*
6. *በየ4-6 ሳምንት ጊዜ ውስጥ በስልጠናህ ለመቀጠል ከመጋቢህ ጋር መገናኘት*
7. *የዓመቱን የመሪዎች የፆምና የፀሎት ጊዜን መካፈል።*
8. *በኃላፊነትህ ሥር ያሉትን እያንዳንዱን ትንንሽ ቡድኖች ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ መጐብኘት።*

## *መሪ*

**ኃላፊነቶቹ**

1. *የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል።*
2. *ለጌታ ሥራ በታማኝነት አስራት ማውጣት።*
3. *የፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾፕን መካፈል።*
4. *የሕይወት ቡድንህን መምራት።*
5. *የህይወት ቡድንህን መምራት ዕጩ የቡድን አባላትን መጐብኘት ወይም መደወል*
6. *ከእያንዳንዱ የህይወት ቡድን ክፍል ጊዜ በፊት ከለማጅ መሪውና ከአስተናጁ ጋር በመሆን ማቀድና መፀለይ*
7. *የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናትን መምራትና ማዛመድ*  (*ወይም ተተኪ መሪውን መመደብ*)

8. የህይወት ቡድኑን ጊዜ መዘጋት
   ሀ/ ማስታወቂያዎችን መናገር
   ለ/ በፀሎት መዘጋት
9. ለእያንዳንዱ ሳምንት ለወንጌል ስርጭት ራዕይንና ማበረታቻ መስጠት
10. ተተኪ መሪህን የአንድ ለአንድ ስልጠናን በሚያስተባብርበት ጊዜ መርዳት
11. በዳይናሚክ ማካፈል ተተኪ መሪህን ማሰልጠን (የወንጌል ጉብኝት ቀጠሮ በወር አንዴ)
12. ተተኪ መሪህን በ «መምራትን መማር» በወር አንዴ ማሰልጠን
13. የመሪዎችን ቡድን ከአሰልጣኝ ጋርና ከሌሎች የቡድን መሪዎች በየ4 ሳምንት መካፈል
14. የዓመቱን የመሪዎች የፆምና የፀሎት ጊዜ መካፈል

# ተተኪ መሪ (በስልጠና ላይ ያለ መሪ)

**ኃላፊነቶቹ**

1. የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል
2. ለጌታ ሥራ በታማኝነት አስራት ማውጣት
3. የፈጣን እድገት ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወርክሾፕን መካፈል
4. የህይወት ቡድን መሪውን መርዳት
5. የህይወት ቡድን አባል ዕጩዎቹን መጐብኘት ወይም ስልክ መደወል
6. ከእያንዳንዱ ስብሰባ በፊት ከመሪህና ከአስተናጋጁ ጋር ለጸሎት መገናኘት
7. የህይወት ቡድኑን ጊዜ መጀመር
- እንግዶችን ማስተዋወቅና እያንዳንዱን ሰው ሰላም ማለት
8. የማካፈል ጊዜውን መምራት (የናሙና የማካፈል ጥያቄዎችን ተመልከት) ወይም ሌላ ሰው መድብ
9. የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜውንና የውይይቱን ጊዜ አልፎ አልፎ በመሪው ጥያቄ መሰረት መምራት
10. የፀሎት ጥያቄዎችን፣ ቤተክርስቲያን አቀፍ ክስተቶችንና ሌሎች መረጃዎችን እንዲለዋወጡ ማድረግ (አልፎ አልፎ ሌላ ሰው ሊመራ ይችላል) እና የፀሎት ጊዜውን መምራት።
11. የቡድኑ አባላት በአንድ ለአንድ ደቀመዝሙርነት ማቀናጀት።
12. ለመምራት መማር የተሰኘውን ስልጠና ለመውሰድ በወር አንዴ ከመሪህ ጋር ተገናኝ።
13. የዳይናሚክ ማካፈል ስልጠናን ለመውሰድ በወር አንዴ ከመሪህ ጋር ተገናኝ
14. ዓመታዊ የመሪዎች ፆምና ፀሎት ጊዜን ተካፈል።

# እንግዳ ተቀባይ

**ኃላፊነቶቹ**

1. የእሁድ የአምልኮ አገልግሎትን በታማኝነት መካፈል።
2. ለጌታ ሥራ በታማኝነት አስራት ማውጣት።
3. ከህይወት ቡድኑ የመገናኛ ሰዓት በፊት ከለማጅ መሪውና ከአስተናጁ ጋር በመሆን መፀለይ
4. ተስማሚ የስብሰባ ቦታና ወንበሮችን በክቡ ማዘጋጀት
5. የህፃን መቀመጫ ካስፈለገ ማዘጋጀት
6. እንግዶችን ሰላም ለማለት ይረዳ ዘንድ ምግቦችን ከስበሰባው ሰዓት በፊት ማሰናዳት
7. የራሳቸውን መፅሀፍ ቅዱስና እስክሪኘቶ ረስተው ለመጡ ይረዳ ዘንድ ተጨማሪ ማዘጋጀት
8. እውነተኛ የሆነ ፍላጐትን ለእያንዳንዱ እንግዳ ማሳየትና ሞቅ ባለ መልካም ሰላምታ ሰላም ማለት
9. የሳምንቱን የተገኙ ሰዎች መቆጣጠሪያ ቅፅ በመጠቀም የተገኙትን ሰዎች መቆጣጠር።
10. በትንሹ ቡድን ጊዜ የእያንዳንዱን በአንድ ለአንድ ስልጠና ውስጥ በሚያሳየው እድገትና እያንዳንዱን ደረጃ በማጠናቀቁ እውቅና ሰጥቶ ማመስገን።

# ማጠቃለያ

የህይወት ቡድንህ ለእያንዳንዱ ተሳታፊ በጣም ጠቃሚ የልምምድ ስፍራ ይሆናል። በቡድኑ የሚታየው ፍቅርና እንክብካቤ ላቅ ላለ ለቁጥርና ለመንፈሳዊ እድገት የተመቸ ሁኔታን ይፈጥራል። እናንተ እንደ ቡድን ቤተሰባችሁን፣ ጐረቤቶቻችሁንና ጓደኞቻችሁን መድረስ ትችላላችሁ። ብዙዎች በክርስቶስ ወዳለው ግንኙነት መጥተው፤ በእምነታቸውና ከቤተክርስቲያን ጋር ባላቸው ህብረት የፀኑ ይሆናሉ። እናንተና የህይወት ቡድናችሁ አካባቢያችሁንና የራሳችሁን ዓለም ለክርስቶስ ልትደርሱ ትችላላችሁ።

ቡድንህ ውጤታማ ይሆንን? መልሱ በእጅህ ነው እግዚአብሔር ጥረትህን ሁሉ ሊባርክ ይወዳል። ደግሞም ይባርካል። በጣም አስደሳችና አስገራሚ ነገር ይሆናል። ሆኖም የተዋጣለት አገልግሎት ለመገንባት ጊዜንና ጥረትን ይጠይቃል። ቁርጠኝነት፣ መስጠትና በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ ያስፈልግሃል። የተለወጡ ህይወቶች ሽልማትህ ይሆናሉ። እግዚአብሔር እየመራህ እያለ ይባርክ!

# የቡድን መመሪያ

1. ሁሉንም ነገር በክርስቶስ ጌትነት ሥር አስገዙ።
   ***«እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያቢሎስን ተቃወሙት ፤ከእናንተም ይሸሻል »*** (ያዕቆብ 4÷7)

2. የሰማችሁት ነገር ሁሉ እዚሁ ይቅር፤ አይውጣ።
   ***«ከቃላት ብዛት ኃጢአት አይታጣም ፤አንደበቱን የሚገታ ግን ጠቢብ ነው።»*** (ምሳሌ 10÷19)

3. ለጌታ እንደሚገባ ኑሩ።
   ***«ብቻ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ ይህ፤ ከሆነ መጥቼ ባያችሁ ወይም በርቀት ሆኜ ስለእናንተ ብሰማ ፣ ለወንጌል እምነት እንደ አንድ ሰው ሆናችሁ በመጋደል በአንድ መንፈስ ፀንታችሁ እንድትቆሙ አውቃለሁ።»*** ፊል 1÷27

4. ግጭቶችን በማስወገድ በውጭ ካሉት ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ ተመላለሱ።
   ***«በውጭ ካሉ ሰዎች ጋር ባላችሁ ግንኙነት በጥበብ ተመላለሱ በተገኘውም ዕድል ሁሉ ተጠቀሙ»*** (ቆላ 4÷5)

5. ሁልጊዜ የመበረታታትን አገልግሎትን ጠብቁ። አድርጉ።
   ***«ስለዚህ በእርግጥ አሁን እንደምታደርጉት ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተፅናኑ ፤ አንዱም ሌላውን ያንፅ።»*** (1ተሰ 5÷11)

6. ጥበብን ተጠቀሙ።
   ***«ከእናንተ ማንም ጥበብ ቢጐድለው፣ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉም የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን? ለእርሱም ይሰጠዋል።»*** (ያዕቆብ 1÷5)

# የሚመሩ መሪዎች

## ክፍል ሁለት

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው፡፡

**የመሪነት ቡድኑን ከመገናኘትህ በፊት ቅድመ ዝግጅት፡-**

☐ 1. ***«የወደፊትህን የህይወት በር መክፈት»*** የተሰኘውን ክፍል አንብብ፡፡ ግንዛቤህንና የፀሎት ህይወትህን ለማካፈል ተዘጋጅ

**ከቡድኑ ጋር በመሆን የሚከናወኑ፡-**

☐ 2. እያንዳንዱ ስለግሉ ደስታና ጭንቀት ያካፍል፡፡ ስለቡድንህ አስፈላጊነትም እንዲሁ

☐ 3. በነጥብ 1 ላይ ከተወያየህ በኋላ ምልክቱን (✓) አድርግበት፡፡ በክርስቶስ መኖር ምን ማለት እንደሆነና እንዴት ይህ ጠቃሚ ዕውነት በህይወት መንገድህ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳመጣ አካፍል፡፡

☐ 4. ከታች ያለውን ሪፖርት ሙላ

**የህይወት ቡድንህ በዚህ ወር እንድትመራ ስልጣን መስጠት፡፡**

☐ 5. ለለማጅህ /ለተተኪ መሪህ/ እና ለህይወት ቡድንህ በግል ለጌታ ያለህን መስጠት አካፍላቸው፡፡

**የህይወት ቡድንህ ሪፖርት**

☐ 6. ________ ሰዎች በመደበኛነት ይሳተፋሉ፡፡

☐ 7. ________ አዳዲስ ተሳታፊዎች በዚህ ባሳለፍነው ወር ተካፍለዋል፡፡

ስም________________________________________

አድራሻ______________________________________

____________________________________________

☐ 8. በአንድ ለአንድ ስልጠና ላይ ያሉ

ዳይናሚክ መሰረታዊን ____________________ __________________ን ያሰለጥናል
____________________ ________________ን ያሰለጥናል

ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ____________________________________ን ያሰለጥናል
የማድረግን

_____________________ ________________ን ያሰለጥናል

ዳይናሚክ ማካፈልን _____________________ ________________ን ያሰለጥናል
____________________ ________________ን ያሰለጥናል

☐ 9. ________ ሰዎች በዚህ ወር በቡድናችን ውስጥ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል፡፡

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 10. እርስ በእርስና ለቡድን አባላቶቻችሁ ፀልዩ፡፡

☐ 11.ወደ ክፍል ሦስት የመልመጃ ዝግጅት አልፈህ ሂድ፡፡

☐ 12.ለሚቀጥለው የሚመሩ መሪዎች ለሚለው ክፍለ ጊዜ ቀን ______________ሰዓት ___________ ቦታ _________________________ መድብ

# የነገህን በር አትዝጋ

የምታያት ዓለም ልክ እንደምታያት ናት። የምታየውንና እንዴት አድርገህ እንደምታያት የሚወስነው ሁልጊዜ አስተሳሰብህ በተገነባበት ነገር ነው። የከዚህ በፊቶቹ ልምምዶችህ ሁሉ ስለራስህና ስለሁኔታዎች ያለህን አተያይ ቀረፀውታል። እነኛን የምታይባቸውን ቅርፆች እስካልቀየርክ ድረስ አተያይህን ልትቀይር አትችልም። አንዳንዶች ህይወትን በሮዝ ቀለም መነፅር ያዩታል። በሌላ መንገድ እንዲያዩት ካስፈለገ፣ መነፅራቸውን መቀየር ያስፈልጋቸዋል። ብዙዎች ህይወትን እንደማትቻል ሆና ያይዋታል። ለእነርሱ እንደዛ ነች፤ እንደምትችል እስከሚያይዋት ድረስ የማትቻል ሆና ትቆያቸዋለች።

እንደ ሰንበት ትምህርት አስተማሪ ትንሹን ጆኒን ***እምነት*** ማለት ምን እንደሆነ ጠይቂው ነበር። ለሦስት ጊዜ ካሰበ በኂላ እንዲህ አለ፣ ***«እምነት ማለት አንድን ነገር፤ እውነት ባይሆንም እንኳ ዕውነት እንደሆነ ማመን ነው»።*** በዚህ ትክክለኛ ባልሆነ ትርጉም ፈገግ የሚሉ ብዙ ክርስቲያኖች እንደሚያምኑ መስለው ይኖራሉ። በእግዚአብሔር ህልውና እንደማያምኑ ሰዎች ሆነው ይኖራሉ። በአንደበታቸው በእግዚአብሔር እንደሚያምኑ ቢናገሩም በየዕለቱ በሚኖሩት ህይወት አለማመናቸውን ያሳያሉ።

ይህ ስልጠና አዳዲስ መነፅሮችን ስለመቀያየር አያወራም ነገር ግን ስለ አዳዲስ ዓይኖች ይናገራል። እውነት ባልሆኑ የውሸት ተስፋዎችን ለማሳመን የማይጥርና የእግዚያብሔርን ቃል በትክክል በማየት እውነት የሆነውን ሁሉ መቀበል ትችል ዘንድ እመኛለሁ። ያንንም ዕውነት፣ እግዚአብሔር ለአንተ ያቀረበልህን ነገር በሙላት በግል ህይወት እንድትለማመደው ምኞቴ ነው።

ሌሎችን ከመምራትህ በፊት፣ በመጀመሪያ የክርስቲያን ህይወት በመኖር መተማመን ሊኖርህ ግድ ነው። እራስህ የማታደርገውን ሌሎች እንዲያደርጉ አትንገራቸው። በተጨማሪም ሰዎች ከአንተ ታማኝና ንፁህ አቋም የሚያንፀባርቅ ህይወት ካላዩ አይከተሉህም።

ይህ ትምህርት የምትሰራውን ስለመቀየር አይደለም። ነገር ግን አንተ በተቀየርክ ጊዜ የምትሰራው ስለመቀየሩ ነው። ሁልጊዜ እውነትን እንደተረዳህበት አይነት ስለራስህና ስላለህበት ሁኔታ አድርግ። በክርስቶስ በሆነው አዲስ የህይወት አቅጣጫ ስለምታደርገውና እንዴት ስለምታደርገው ነገር ለመለወጥ የሚያስችልህን ብቃት ስታሳድግ ለማየት ዝግጁ ነን ። አንተም በትክክል ማሰብህን ለመቀጠልና አዳዲስ ብቃቶችን ተግባራዊ ለማድረግ በተጠያቂነትህ ለመቀጠል እርዳታ ያስፈልግህ ይሆናል።

## ከቀድሞ ህይወቴ ነፃ አውጣኝ

***«ብቻ ከታሰርኩበት አሮጌ ህይወት ነፃ ብወጣ» ወይም «ላለመስራት እየሞከርኩ ነው» «እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ህይወት ለመኖር ብፈልግም ነገር ግን ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም ሁሉንም ነገር እየሞከርኩ ነው።» ወይም «አንድ የማደረገው ነገር መኖር አለበት»*** ይህ እግዚአብሔርን ከሚፈሩ የዋህ ክርስቲያኖች ተስፋ ከመቁረጥ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ናቸው። ችግሩ የጭንቀታቸው መሰረት ያለው በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ያገኙበትን መሰረት አለመቀበላቸው ወይም አለማወቃቸው ላይ ነው። በራሳቸው ተስፋ ማጣታቸው በራሳቸው እምነት እንደነበራቸው ያሳያል። አሁን ከባለፈውና ከአሁን ሥራቸው በመነሳት ራሳቸውን ለመቀበል ሲቸገሩ ይታያሉ።

***ለምን ንፁሁና ቅዱሱ አምላክ እኔን ተቀበለ?*** እርሱ ከእኛ የሚጠበቀውንና የሚያስፈልገውን ነገር እንደሌለን ጠንቅቆ ያውቃል። ይህ ጉዳይ በጣም አስደንጋጭ የሆነበት ምክንያት ለእኛ ደህና መሆን በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ነው። በእግዚአብሔር እንደተቀበልን ማወቅ ይኖርብናል። እራስን አለመቀበልና በሌሎች መቀበልህን መጠራጠር ***በእግዚአብሔር ተቀባይነት አላገኘሁም ብሎ መገመት ነው።***

ይህንን ጉዳይ በጉልበት በአንተ ውስጥ ማስገባት አልፈልግም፤ ነገር ግን ምንም እንኳን ቁጥራቸው የበዛ ብዙ ነገሮች ለእግዚአብሔር ብታደርግም፣ ተቀባይነትን በእግዚአብሔር አያስገኝልህም። ኢሳያስ 64÷6 እንዲህ ይላል ***«የጽድቅ ሥራችን እንደ መርገም ጨርቅ ነው።»*** ይህ ጥቅስ በጣም ክፉ ስለሆነው ባህሪይህ የተነገር አይደለም፤ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ምርጥ ነው ብለህ ስለሰራኸው ነገር እንጂ። ልክ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ ይመስላል። ***«እባክህ በበጐ ሥራህ እኔን ለማስገረም አትሞክር።»*** እስቲ

አስብበት እግዚአብሔር ለራሱ የተሻለ ነገር ለመስራት ሳይችል እንደቀረና አንተ ለእግዚአብሔር ምንም አንዳች ነገር ማድረግ እንደምትችል በእርግጥ ታስባለህ? እናም እንዲህ ትላለህ፣ «*የመሞከር ጥቅሙ ምንድነው?*» በትክክል መሞከር ምንም ጥቅም የለውም። እግዚአብሔር የአንተን የመርገም ጨርቅ የሆነ ጥረትህን አይቀበልም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ***በሚወደው በእርሱ በኩል*** ይቀበልሃል። (ኤፌሶን 1÷6) በክርስቶስ ተቀባይነትንና መወደድን አግኝቻለሁ ምክንያቱም ክርስቶስ በአብ መወደድንና ተቀባይነት ስላገኘ። እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ሰላም አድርጓል ምክንያቱም ኢየሱስ ***«በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደሙ ሰላምን አድርጓል»*** (ቄላሲያስ 1÷20) ይሄ እግዚአብሔር ያቀረበው ብቸኛ መንገድ ነው። ከርሱ መንገድ ውጪ ሌላ መንገድ የለም።

ክርስቶስ ለኃጢአታችን ሞተ። ብዙዎች ይህን የተገነዘቡ ኢየሱስ ክርስቶስ ያፈሰሰውን ደም እንደ ኃጥያታቸው መቀጫ ሙሉ ክፍያ ቀድመው ተቀብለዋል። ለኃጢአቶችህ ሁሉ ይቅርታን እንዳገኘህ አውቀህ፣ ነገር ግን የቀረ አለ ብሎ መጠበቅ፣ ምንኛ አስገራሚ ነገር ነው! የወንጌሉ ምርጥ ክፍል ሳይነገር ቀርቷል። እውነት ነው ክርስቶስ የእኔን ኃጢአያት ተሸክሞ ስለእኔ ኃጢያት ሲል ሞቷል። ነገር ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሲሞት ከእኔ ጋር ነው የሞተው። ብዙ ሰዎች የኃጢአት ይቅርታ ለማግኘት ምንም አይነት ነገር ማድረግ እንደሌለብህና በቀላሉ የክርስቶስን ሞት እንደ ሙሉ ክፍያ መቀበል ግድ እንደሆነ በሙሉ ልብ ያስተምራሉ። በቅዱስ አምላክ ፊት ንፁህ መሆንን ከማወቅ አዲስ ማንነት አለኝ። ኃጢአት አልባ የሆነ አይደለም።

ብዙ ጊዜ እነዚሁ ሰዎች እግዚአብሔር ስላደረገልህ እርሱን ለማክበር እንደምላሽ ልታደርገው የምትችለው ትንሽ ነገር ለእግዚአብሔር ለመኖር መሞከር ነው ብለው ያነቃቁሃል። አደለም የኔ ወንድም ልክ የኃጢአት ይቅርታህን በሙከራ እንዳላገኘህ ሁሉ በህይወትህን በሙከራ መኖር አትችልም። በክርስቶስ ያለውን አዲስ ህይወት በእምነት ተቀብለናል። ***«ከመለኮታዊ ባሕሪይ ተካፋዮች»*** እንድንሆን በእምነት በእርሱ ውስጥ ደግሞ ተወልደናል። (ጴጥሮስ 1÷4)

የእኛ ድርሻ አሁን ባገኘነው ህይወት በሙላት እንድንኖር መማር ነው። ይህም በውስጣችን ያለውን የእግዚያብሔር ህይወት እንድንረዳ፣ በእለት ተዕለት ኑሮአችን ውስጥ የእርሱን ህይወት እንድንለማመድ በእግዚያብሔር አምነን በኃይል ለመሞላት፣ እግዚያብሔር የእርሱን ህይወት ባህርይ በእኛ ህይወት ውስጥ ለማሳደግ በሚያስፈልገን ጊዜ ትዕግስት እንዲኖረን መፅሀፍ ቅዱስን ማጥናት ይጠይቃል። አስታውስ በፊልጵስዩስ 2÷13 ***«...እንደ በጎ ፋቃዱ በእናንተ ውስጥ የሚሰራ እግዚያብሔር ነውና»*** ተብለናል። በእኛ ውስጥ የሚደረገው የእርሱ በጐ ፈቃድ ምንድን ነው? ሁሉንም ነገር ለዚህ አንድ አላማ ሲል ይሰራል። ***«የኢየሱስ ህይወት ሟች በሆነው ሥጋችን እንዲገለጥ ...»*** (2ቆሮንቶስ 4÷11)ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ ***«ይሄ ህይወት ነው ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው...»*** (ፊልጵስዩስ 1÷2) ይህ ጥበብ «**ፅድቅን በሚራቡና በሚጠሙ**» ሰዎች ብቻ ይመጣል።

## *በራሴ የራስ ህይወት በማልረካበት ግዜ የእግዚያብሔርን ህይወት ብቻ እመኛለሁ (ማድረግ የምችለው ምርጡ ነገር)*

እንዴት ነው እግዚያብሔር የራሳችንን የግል ህይወት እስክንተው ድረስ ተስፋ እንድንቆርጥ የሚያደርገን? በቀላሉ ራሳችን እንድንመለከት ይተወናል፤ በትክክል ምን መሆናችንን የራሳችንን ውድቀት እንደመሆንዲስ እየተጠቆመ ምን ያህል እንደምናስጠላ ያሳየናል። የእግዚያብሔር ቃል ለጉድለታችን በቂ መሆኑ ግልፅ ነው፤ ነገር ግነ እኔነትን በተቻለን ሁሉ ለመጠበቅ መፈለጋችን ምክንያትና የራሳችን ተሞክሮ ወደ ነበርንበት ህይወት ይመሩናል። እነዚህ መራራ የህይወት ልምምዶች ብዙውን ጊዜ በጣም ያስቃያሉ ከሰዎች ማስታገሻ ለማግኘትና ለመፅናናት በደንብ የተዘጋጀ ጓደኛ እስከ ሚያስፈልገን ድረስ። ማፅናናታቸው እኔን ለመጠገን ነው። እኔን ከመስቀሉ ላይ ማውረድ ነው። በዚህ ቦታ መገኘቴ ምንም እንዳይደለ ለማፅናናት። ሆኖም እግዚአብሔር በማያቋርጠው ፀጋው እኔ ያልሰራሁትን ሊያጠናቅቅ

እንደገና ይጀምራል። እግዚአብሔርን ለማድከም ሳይሆን ለመሞት ወደ መስቀሉ አመጣኝ። እየሞትኩ እንድሄድም እንኳ ሳይሆን ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ወደ ሙሉና የመጨረሻ ሞት ከክርስቶስ ጋር በመስቀል እገባለሁ። ለምን ቢባል ***«ከእንግዲህ እኔ አልኖርም»*** የሚለውን እስከማውቅ ድረስ የእርሱን አስደናቂ ህይወት ***«ክርስቶስ በውስጤ ይኖራል»*** በፍፁም  አላውቀውም። (*ገላትያ* 2÷20)

***ለእኔነት እንዴት መሞት እችላለሁ?*** ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። አታውቅም በቀላሉ እግዚያብሔር በቃሉ የሚለውን ተቀበል ***«ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንድንሆን የተጠመቅን ከሞቱ ጋር አንድ እንድንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን?ስለዚህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሞት እንደተነሳ እኛም ምክንያቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ለኃጢያት እንደሞተ*** (ሮሜ 6÷6-7) እንዲሁ አንተም ለኃጥያት ሞተሃል፣***«በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል»*** (ቆላስያስ 2÷10)

ለኃጥያት መሞቴን ለመቀበል እንዴት እንደተቸገርኩ አስታውሳለሁ። ከተወሰኑ አመታት በፊት አንድን ወጣት በሮሜ 6 ላይ መፅሀፍ ቅዱስ አስተምር ነበር። ይህ ዕውነት ለእኔ አንዳልገባኝ መቀበሌ ግልፅ ነበር ምክንያቱም ልምምዴ ለኃጥያት እንዳልሞትኩ ያሳብቅብኝ ነበር። ይህንን በእነርሱ ፊት መቀበሌ አስጨንቆኝ ነበር። ወደ ቤትም ሄጄ ሮሜ 6÷6 ደጋግሜ አንብቤው ነበር። ለእግዚያብሔርም እንዲህ አልኩት፣ «ለኃጥያት አልሞትኩም።» ሳነበው ደግሞ እግዚአብሔር እንዲህ ይለኛል «ለኃጥያት ሞተሃል» ወደ ጥልቅ ማጠቃለያ እስክመጣ ድረሰ ወደ ፊትና ወደኋላ ለበርካታ ጊዜ ሄደንበታል። ምክንያቱም እኔና እግዚያብሔር አልተስማማንም ነበር። አንዳችን ዋሽተን ነበር። አሁን ማን እንደዋሸና ማን እውነት ተናግሮ እንደነበረ ብዙ ጊዜም አልወሰደብኝም ነበር። ታያላችሁ ምክንያቱም በተፈጥሮዬ ኃጥያተኛ ነኝ ብዬ ስለወሰንኩ /ስለደመደምኩ/ እስከዛ ድረስ ለኃጥያት ተገዢ እንደነበርኩ አምኜ ኃጥያተኛ እንደሆነ ሰው እኖር ነበር። እግዜአብሔርን ሳምንና ለኃጥያት መሞቴን የሚገልፅለኝን ቃሉን ስቀበል በኃጥያት ላይ ድል አግኝቼ መኖር ችያለሁ። እራሴን ለኃጥያት በክርስቶስ እንደ ሞተ ሰው መቁጠሬ እውነት አላደረገውም ቀድሞውንም ቢሆን እውነት ነው። እምነት እንጂ በልምምድን ማመን አይደለም። ከእግዜአብሔር ከሚገኝ እምነት ውጪ አስተማማኝ የሆነ ድል አይኖርም። በዚህ ጉዳይ ላይ ጀምስ ማክኮኒኪይ እንዲህ ፅፈዋል።

***«እምነት በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ ነው።***<br>***እናም ይህ በእግዚአብሔር መደገፍ የሚጀምረው***<br>***በራስ መደገፍ ላይ ሲያበቃ ብቻ ነው»***

አንዴ እዚህን እውነቶች መቁጠር ከጀመርን፣ እግዚያአብሔር አባታችን በእምነት ሊያሳድገን ይጀምራል። ጆርጅ ሙለር እንዲህ ለማለት ችሎ ነበር። **እግዚያአብሔር የልጆቹን እምነት ማሳደግ ደስ ይለዋል ከድል በፊት ምንም አይነት ፈተናንና ትዕግስትንም ያለምንም ድካም ከመፈለግ ይልቅ ለእድገታችን እንደ መንገድ ወስደናቸው ልነቀበላቸው ይገባናል ። ሆን ብዬ እናገራለሁ ፈተናዎች፣ መሰናክሎች፣ አስቸጋሪ ሁኔታዎችና አንዳንድ ሽንፈቶች የእምነት ማጠንከሪያዎች ናቸው።**

ስለዚህ፦ ***«ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገሩ ሰዎች አድርጋችሁ ራሳችሁን ለእግዚያአብሔር አቅርቡ»*** (ሮሜ 6÷13)

*መገዛት*

*መገዛት መሞት ነው። ለፍቃዴ መሞት፣ ለራስ መንገድ መሞት ወይም ለማንኛው ውድ ለምለው ነገር መሞት ነው። ሞትን እንደ መጨረሻ ፍፃሜ ካላየነው፣ አሉታዊና የማያስፈልግ ይሆናል። ነገርግን እግዚአብሔር በዛ መንገድ አያየውም፤ ለርሱ ሞት እኛን በርሱ ውስጥ አሳልፎ ወደ ህይወት ማለትም ወደ እርሱ ህይወት ለማምጣት የማይቀር በር ነው። ደግሞም የዘወትር መፅሀፍ ቅዱሳዊ ርዕስ ነው።*

ዮሐንስ 12÷24 ***«የስንዴ ቅንጣት መሬት ላይ ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።»***

በገላትያ 2÷20 ላይ እንደተቀመጠው በመጀመሪያ ***«እኔ አልኖርም»***ን መለማመድ ይኖርብናል፤ ***«ነገር ግን ክርስቶስን»*** ከመለማመዳችን በፊት። ይህ የእግዚአብሔር አሰራር ነው።

*ታሪኩ ስለአንድ ጥጃ ይናገራል። በተወለደ ጊዜ ማንኛውንም ነገር ማለትም ወተት ፍቅርና እንክብካቤ ያገኝ ነበር። ለእርሱ ህይወት ቀላልና አስደሳች ነበር። ቀኑን ሙሉ ከሌሎች ጥጆች ጋር በመሮጥና በመጫወት ያሳልፍ ነበር። ሆኖም አንድ ቀን በጣም እስኪገረምና እስኪደነገጥ ድረስ ገበሬው ከአንድ ትልቅ በሬ ጋር ጭንቅላቱን በኃይል ቀንበር እንዲሸከም አድርጐ ጠመደው። ረጅሙ በሬ ሲሄድ እርሱም መሄዱ ግድ ነበር። መሬቱን እንኳ በጥቂቱ ነበር ይነካ የነበረው። በመጀመሪያ ከዚያ ከማያመቸው ሁኔታ ለመውጣት ተወራጨ፤ ነገር ግን ምንም አልረዳውም። ለእርሱ ይሄ ሁሉ ምንም ትርጉም አልነበረው። ሆኖም ለወደፊት እያዘጋጀው ላለው ገበሬ ግን ትክክለኛ ትርጉም ነበረው።*

*ልክ እንደ ወጣቱ ጥጃ እኛም እግዚአብሔር በህይወታችን የሚሰራውን እንጠይቃለን፣ እንፈራገጣለን፣እንጮሃለን፣እንተቻለንም። በዚህ ሁሉ ማጉረምረም እግዚአብሔር ግን ለእኛ ያለውን የመንፈሳዊ ዕድገት አጀንዳ እንደቀጠለ ነው። ልክ እንደሚያስፈልገን እግዚአብሔር እያደረገ ነው። ለሚሻል የነገ ስራ እያዘጋጀን እንዳለ ስናውቅ እናመሰግነዋለን። እርሱን ካለመተባበር ይልቅ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን። ልክ ልጁን እንደሚወድ ወላጅ እድገታችን ሙሉና ትርጉም ያለው እንዲሆን ይንከባከበናል። ከእኔነት አለም እያወጣን ነው- «በእኔ ማለትም ኃጢያተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ ውስጥ ምንም በጐ ነገር እንደማይኖር ዐውቃለሁ»*(ሮሜ 7 ÷ 8) *በደስታ «ለኔ መኖር ክርስቶስ ነው»*(ፊልጵስዩስ1÷21) *ወደ ምንልበት ስፍራ ያወጣናል።*

*ራስህን እንደ ህያው መስዋዕት ለእግዚአብሔር ልታስገዛ ፍቃደኛ ነህ? እስካሁን ይህንን እስካላደረግህ ድረስ እርሱን ለማገልገል መሞከርህ ትርጉም የለውም። ይሄ የወደፊት ህይወት በርህን መክፈት ነው። ይሄንን እስካሁን እስካላደረግህ ድረስ የአገልግሎትን ጣዕም ልታውቅ አትችልም።*

*ለጌታ መገኘትህን በወረቀት ላይ በመፃፍ ግለፅለት*

ጌታኢየሱስ

________________________________________

________________________________________

________________________________________

________________________________________

*ፊርማ* ________________________

*ቀን* ________________________

# የሚመሩ መሪዎች

## ክፍል ሦስት

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው፡፡

**የመሪነት ቡድኑን ከማገናኘትህ በፊት ቅድመዝግጅት፡-**

☐ 1. የመሪ ኃላፊነት የሚለውን አንብብና በአራቱ ኃላፊነቶች ላይ ለመወያየት ተዘጋጅ፡፡

☐ 2. **ለውጤታማ ሰዎች የአፈፃፀም ሂደት** የሚለውን ክፍል ጥናት አጠናቅቅ፡፡ ይህ ጠቃሚ ጥናት የተወሰነ ሰዓት ሊወስድ ይችላል፤ ነገር ግን ይገባዋል፡፡ ከመሪነት ቡድኑ ጋር መልሶችህን ለማካፈልና ለመወያየት ተዘጋጅ፡፡

☐ 3. ከዚህ በታች ያለውን ሪፖርት አጠናቅ፡፡

**ከመሪ ቡድኑ ጋር በመሆን የሚፈጸም፡-**

☐ 4. እያንዳንዱ ስለግሉ ደስታና ጭንቀት ያካፍል፡፡ ስለቡድንህ አስፈላጊነትም እንዲሁ

☐ 5. ከነጥብ 1-3 ላይ ከተወያየህ በኋላ ምልክቱን (✓) አድርግበት፡፡ በክርስቶስ መኖር ምን ማለት እንደሆነና እንዴት ይህ ጠቃሚ ዕውነት በህይወት መንገድህ ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ እንዳመጣ አካፍል፡፡

☐ 6. ከአራቱ ብርቱ የሆነው ኃላፊነቴ ________________________________

ከአራቱ ደካማ  የሆነው ኃላፊነቴ________________________________

ፀልይልኝ________________________________________

________________________________________________

☐ 7. ለቀጣይ የወደፊት ጉዞ ይረዳህ ዘንድ ከሰባቱ ደረጃዎች የትኛውን አከበብክ፡፡ ምን ልታደረግ አቅደሃል?

እቅዴ________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

**የህይወት ቡድንህ ሪፖሪት**

☐ 8. _________ ሰዎች በመደበኛነት ይሳተፋሉ።

☐ 9. ________ አዳዲስ ተሳታፊዎች በዚህ ባሳለፍነው ወር ተካፍለዋል።
ስም______________________________________________

አድራሻ____________________________________________

_________________________________________________

☐ 10. በአንድ ለአንድ ስልጠና ላይ ያሉ

ዳይናሚክ መሰረታዊን ____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግን ________________________________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
ዳይናሚክ ማካፈልን ____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል

☐ 11. _________ ሰዎች በዚህ ወር በቡድናችን ውስጥ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል።

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 12. እርስ በእርስና ለቡድን አባላቶቻችሁ ፀልዩ።

☐ 13. ወደ ክፍል ሶስት የመልመጃ ዝግጅት አልፈህ ሂድ።

☐ 14.ለሚቀጥለው የሚመሩ መሪዎች ለሚለው ክፍለግዜ ቀን_______________ ሰዓት ____________________ ቦታ ______________________ መድብ

# የህይወት ቡድኑ መሪ ኃላፊነቶች

በህይወት ቡድኑ መሪ ህይወት ውስጥ አራት መሰረታዊ ኃላፊነቶች አሉ። ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቃሉ፣ ለእግዚአብሔር ህዝቡ፣ ለጠፉትና ለስራው ከፍተኛ ፍቅርና መሰጠት ሊኖረው የግድ ነው። መሪው ክርስቶስን ማዕከል ያላደረገ ከሆነ፣ ቡድኑ ለሐሰተኛ እምነቶችና ልምምዶች የተጋለጠ ይሆናል። ለክርስቶስ አካል ፍቅርና መሰጠት ከሌለው፣ አንድም በቡድኑ ውስጥ ላሉት ግድ የለውም አልያም ደግሞ ቤተክርስቲያንን መገንባቱን ይተውና የራሱን ትንሽ መንግስት በትንሹ ቡድን ሊመሰርት ይሞክራል። ላልዳኑት ሰዎች ግድ ከሌለው፣ ቡድኑ የጠፉትን ለማዳን ያላደገና የወደቀ ይሆናል። ለተሰጠው የወንጌል ተልዕኮ ተግባር ማለት የታላቁን ተልዕኮ ዕውን ከማድረግ አንፃር ታማኝ ካልሆነ፣ ቡድኑን ላያዘጋጀው ይችላል።

### 1. ለኢየሱስ ክርስቶስና ለቃሉ የፀና ፍቅር እና መሰጠት

መሪው በህይወቱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች የሚታዩበት ክርስቶስን ማዕከሉ ያደረገ መሆን አለበት። ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ባለው ግንኙነት ለማደግ ፍላጐት ሊኖረውና ራሱን ደቀመዝሙር ለማድረግ በየቀኑ በፀሎትና መፅሀፍ ቅዱስን በማጥናት ከእርሱ ጋር ጊዜ የሚወስድ መሆን አለበት።

### 2. ለእግዚአብሔር ህዝብ የፀና ፍቅር እና መሰጠት

ተነሳሽነቱን መሪው መውሰድ አለበት። መሪ የሚመራ ነው ተብሏል። ስለሆነም አንድ ነገር እስኪሆን መጠበቅ የለበትም ወይም የሆነ ነገር እስኪከሰት ተስፋ አያደርግም ነገርግን እንዲከሰት ያደረገዋል። ለቡድኑ በቡርቱ የሚያስብና የሚሰማው ሰው መሆን አለበት። «በመንፈሳዊ ህይወታቸው የት ደረሱ? ለቃሉ እየታዘዙ መጥተዋል? ለአገልግሎት እየተዘጋጁ ነው?» እያለ ይህንን አይነት ህይወት ለማምጣት ፈጣሪና ቅን መሆን አለበት። በቃል ሳይሆን በተግባር ለቡድኑ ምሳሌ መሆን አለበት። መሪው በግሉ ጊዜ ወስዶ ከጌታ ጋር የማያሳልፍ ከሆነ እንዴት ቡድኑን ይመራል ተብሎ ይጠበቃል? በቡድኑ አባላት ህይወት ውስጥ እየገባ ሲሄድ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ያውቅና የቡድኑን ተግር ለመፍታት ሊረዳቸውና ሊያፅናናቸው ይችላል። ለእያንዳንዱ የቡድን አባላት አሳቢ አፍቃሪ ሆኖ በመገለጥ፣ ግልፅነትንና የሞቀ የጉባኤ ሁኔታ መፍጠር አለበት። ሰዎች በመሪው ላይ ሳይሆን የበለጠ በኢየሱስ ክርስቶስ ላየ እንዲደገፉ ለማገልገል ይጓጓል።

### 3. ለጠፉት ነፍሳት የፀና ፍቅር እና መሰጠት

ክርስቶስን ለማያውቁት ሰዎች መሰጠት ይችል ዘንድ፣ ክርስቶስ በመስቀል ላየ የሰራውን ስራ ሁልጊዜ በድፍረት ሌሎች በማካፈል ምሳሌ ሊሆን ይገባዋል። እንደገናም ሰዎቹን በሚኖሩበትና በሚሰሩበት መድረስ ይችሉ ዘንድ በትጋት ማዘጋጀትና ማነሳሳት አለበት። ለወንጌል ስርጭቱ ጊዜ እስካልተመቻቸ ድረስ ቡድኑ ዝምብሎ አንድ ቦታ የተከማቸና እርስ በርሱ የሚሚሚቅ ነው የሚሆነው።

### 4. ለስራ ፍቅር እና መሰጠት

መሪው በህይወት ቡድኑ ውስጥ ላለው ስራና ከክርስቶስ ለተቀበለው ተልዕኮ ታማኝ መሆን አለበት። ቡድኑን የጠፋው አለም ለመዋጀት ተልዕኮ ያለው የእግዚአብሔር ህዝብ እንዲሆን በመምራቱ ሂደት የተዋጣለት ስራ ይሰራ ዘንድ፤ ከሌሎች ለመማር ፍቃደኛ የሆነና ለመማር የሚፈልግ ልብ ያለው መሆን አለበት።

# የውጤታማ ሰዎች የአፈፃፀም ሂደት

የአፈፃፀሙ ሂደት በሰባት ደረጃ ይከፋፈላል፡-

1. በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት።
2. ፍላጐትና ራዕይ
3. ግቦች
4. ዕቅድ ማውጣት
5. ተግባር
6. እምነት
7. ስራ

**ነህሞያ እንዴት ይህን የአፈፃፀም ሂደት እንደተከተለ ለማየትየነህምያን መፅሀፍ ከምዕራፍ 1-3 አንብብ**

**ደረጃ አንድ፡- በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት።**

> ***«እምነት ተስፋ ያደረገነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውንም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው፡፡»*** (ዕብራውያን 11÷1)

እንደገናም የእግዚአብሔርን ህልውና እና ኃይሉን ያለምንም ጥያቄ እውቅና የምንሰጥበት ድርጊት ነው፡፡ አንድ ሰው አንድ ግዜ እንዲህ ብሎ ነበር፣ ***«ሊሆኑ በሚችሉ ነገሮች ብቻ ማመን እምነት ሳይሆን ፍልስፍና ነው፡፡»*** እግዜአብሔር ላይ ካለ እምነት ውጪ ዘላለማዊ ክንውን አይኖርም፡፡

በነህምያ 1÷5-12 ባለው የነህምያ ፀሎት፣ ለፀሎቱ መተማመኛ የሰጠው ስለኢየሩሳሌም የሰማው ነገር ምን ነበር?

______________________________________________

______________________________________________

______________________________________________

አምናለሁ እግዚአብሔር ☐ እንደሚችል ☐ ምናልባት ☐ በውስጤ እርሱን እንዳከብር ያስቀመጠውን መሻት ወደፊት ያደርገዋል፡፡

**ደረጃ ሁለት፡- ፍላጐትና ራዕይ /ህልም/**

«ለምንድነው አንዳንዶች የሚሳካላቸው ሌሎች የማይሳካላቸው» የሚለው ጥያቄ የተለመደ ጥያቄ ነው፡፡ ይሄን ለማወቅ ጥናት ያደረጉና ውጤታማ የሆኑ አጥኚዎች በርካታ ምክንያቶችን ጠቁመዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ስኬታማ የሆኑበት ምክንያት አላሚዎች ስለሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚወደውንና ለመያዝ የሚፈልገውን ያልማሉ፡፡ በህልማቸው ላይ ያተኩራሉ፣ ይጠብቁታል፣ ይንከባከቡታል፡፡ ውጤታማ ሰዎች ነገሮችን በአዕምሮ ውስጥ እስከሚችሉት ድረስ መቅረፅን ይወዳሉ፡፡ የእኛ ምኞት እግዚአብሔር የሚያልመውን ማለም መቻላችን እንዲሁም ወደ መሆን እንዲመጣ መወሰናችን በህይወት እያለን ለምናከናውናቸው ነገሮች ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ ማንም ሰው በውስጥህ ያለውን የእግዚአብሔር ህልም ከውስጥህ እንዲሰርቅህ አትፍቀድ፡፡

ንጉስ አርጤክስስን ለማናገር በቀረበ ጊዜ ህልሙ ምን ያህል በነህምያ ልብ ውስጥ ግልፅ ነበር? ነህምያ2÷4-8______________________________________

______________________________________________

______________________________________________

ያለምንም ውሱንነት እግዚአብሔር የህይወት ቡድንህ አገልግሎት ምን መሆን እንዳለበት እንደሚፈልግ ያለህን እምነት ግለፅ። በሦስት ዓመት ውስጥ ምን ሊሆን ሊመስል ይችላል?

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

እግዚአብሔር ብቻ ሊያደርገው የሚችለው ምን የግል ፍላጐት አለህ? ____________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

**ደረጃ ክፍል ሦስት - ግቦች**

ማለም የተፈጥሮ የህይወት ክፍል ነው። ስለምንመኘው ነገር እናልማለን። ምኞታችን ግልፅ ሲሆን ህልማችንም ግልፅ ይሆናል። እናም ግቦችን በጣም ግልፅ በሆነ መልኩ እናስቀምጣለን። ምኞት አንቀሳቃሽ ነው ለምንፈፅመው ስራ ሁሉ መወርወሪያ ነው። በምኞት ላይና ግልፅ ባልሆነ ህልም ላይ ትኩረት ማድረግ የተለዩ ግቦች እንዲከሰቱ ያደርጋል።

ኢየሩሳሌምን መልሶ ለመገንባት ሊወሰድ የሚችለውን በምናቡ ካየ በኋላ ነህምያ ምን ነበር

ያደረገው? ነህምያ 2÷6-9 ________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ፍላጐትህ ለመፈፀም ምን ያስፈልግሃል?
3 የቡድን ግቦች ና 3 የግል ግቦችን ዘርዝር።

| **የቡድን ግቦች** | **የግል ግቦች** |
| --- | --- |
| የአንድ ወር ____________________ | ____________________ |
| ____________________ | ____________________ |
| የስድስት ወሮች ____________________ | ____________________ |
| ____________________ | ____________________ |
| የሦስት ዓመት ____________________ | ____________________ |
| ____________________ | ____________________ |

**ደረጃ አራት፡ - እቅድ ማውጣት**
ህልም ያለ ዕቅድ የማይሆን የህልም አለም ሐሳብ ነው። ሰዎች የወደቁት ለዕቅድ ማውጣት ስለወደቁ ነው ያልወደቁበትም ምክንያት ለማቀድ ስላልወደቁ ነው። ያሰቡበት ለመድረስና ለመከናወን እቅድ ወሳኝ ነው። ስለሆነም የጊዜ ሰሌዳ ለሂደቱ ወሳኝ ግብዓት ነው። የት እንደምትሄድ ካላወቅህ ጉዞን ማቀድ አስቸጋሪ ነው። ለዚህ ነው ከማቀድ በፊት ግቦችን ማስቀመጥ ያስፈለገው።

ነህምያ ኢየሩሳሌምን ባየ ግዜ ምንድን ነበር ያደረገው? ነህምያ 2÷11-6

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ግቦችህን እውን ለማድረግ ምን ማድረግ ያስፈልግሃል? 3 ደረጃዎችን ከሚጠናቀቁበት ቀን ጋር አስፋር፡፡

የህይወት ቡድን ግቦች ዕውን ለማድረግ ያለኝ ዕቅድ

1. ______________________________________ ቀን ________________
2. ______________________________________ ቀን ________________
3. ______________________________________ ቀን ________________

የግል ግቦቼን ዕውን ለማድረግ ያለኝ ዕቅድ

1. ______________________________________ ቀን ________________
2. ______________________________________ ቀን ________________
3. ______________________________________ ቀን ________________

**ደረጃ አምስት - ክንውን**

ሁሉም ህልሞችህ ፣ግቦችህና ዕቅዶችህ ውጤት በሚያወጣ ክንውን ካልታገዙ ሊተኑ ይችላሉ፡፡ መወሰን ያለብህ ነገር ሊኖር በምኞቶችህ ላይ ተግባራዊ እርምጃ ለመውሰድ ከምር መነሳት ነው፡፡

ነህምያ እቅዱን ለህዝቡ ባካፈለ ጊዜ፣ የሕዝቡ ምላሽ እንዴት ነበር? ነህምያ 2÷17-18

______________________________________________________________

______________________________________________________________

______________________________________________________________

ለማን ነው ህልሞችህን ዕቅዶችህንና ግቦችህን መንገር ያለብህ? ________________________

______________________________________________________________

የእነርሱ ተሳትፎ ያስፈለግሃል? ____________ አዎ ____________ አያስፈልገኝም ምን ማድረግ አለባቸው? ______________________________________________

______________________________________________________________

**ደረጃ ስድስት ፡- እምነት (ለማድረግ ፍቃድ)**

እምነት ተግባራዊ እርምጃ የሚቀድምና የሚያጅብ መሆን አለበት፡፡ የስኬት በጣም አስቸጋሪው ነገር ማድረግ እንደምትችል ማመንህና የእግዚአብሔር ፍቃድና የሌሎችን (ቤተሰብ መጋቢ ወ.ዘ.ተ) ማረጋገጫ አገኛለሁ ብሎ ማመኑ ነው፡፡

ከሁለት እስከ አምስት ያሉት የአፈፃፀም ሂደት ደረጃዎች በግልፅ ማስረዳት የሚቻልና በአፅምሮአችን ልንገነዘባቸው እንችላለን ነገር ግን እምነት ከስሜታችን ጋር ይያያዛል፡፡ አብሮ ይሄዳል፡፡ የተገለፀን/የተብራራን ነገር መያዝ የሰው ተፈጥሮ ነው፡፡ እርግጠኛ ባልሆንበት ነገር ምቾት አይሰማንም፡፡

ሆኖም የሆነ ነገር እንደምንሰራ ባናምን፣ የእምነታችን መታጣት በራሱ በርትተን እንዳንሰራ ያደርገናል እናም ይህ የስራ እጥረት ደግሞ ዕድላችንን ይወስነዋል፡፡ በተደጋጋሚ ጊዜ ለራሳችን አደገኛ ጠላት ሆነን እንገኛለን፡፡ ብዙ ጊዜ የምናውቀውንና የሚመችንን ስራ በትጋት ለመስራት እናዘነብላለን፡፡ ይሄ እንደተለመደው ከመለኮታዊ አሰራር የሚመጣ አይደለም፡፡
የእግዚአብሔር ህልም ማለም አነቃቂና አስደሳች ነው፡፡ ህልሞች ዕውን እንዲሆኑ ግቦችንና ዕቅዶችን ይወልዳል፡፡ ሆኖም ተግባር በእግዚአብሔር ችሎታ መሰረት እንደምንችል እስከምናምን ድረስ ተግባር በጭራሽ አይከሰትም፡፡

***እምነት የተግባር ማነሳሻ ነው፡፡***

***መፍቀድ ፍርሃቷን እንደምትጥል፣ የእግዚአብሔርን የማይታየውን ጠጣር አየር ለመጨረሻ ጊዜ ለመታመንና የራሷን ያልተገራ ክንፍ ለአዲስ በከፍታ ለሚንሳፈፍ ህይወት ዝግጁ እንደምትሆን፣ በሰማይና በመሬት መካከል ለመኖር እንደተገባው እና ከጐጆዋ ጫፍ ላይ ለመጨረሻ ጊዜ ቁልቁል እንደምታይ የንሰር ጫጩት ነው፡፡***

*ሪቻርድ ግሬይሎርድ ብሪሌይ*

***«እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ... እንደንስር በክንፍ ይወጣሉ»*** ኢሳይያስ 40÷31

የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልክተህ እያንዳንዱን የ "ሀ"ንና የ"ለ"ን ጥያቄዎች መልስ
ሀ/ የእየሩሳሌምን የእነደገና መገንባት ስራ እንዳይሰራ የጠላቶቻቸው ስልቶች ምን ነበሩ?
ለ/ የነህምያ ምላሽ እንዴት ነበር?

ሀ/ 2÷9 ______________________________

ለ/ 2÷20 ______________________________

ሀ/ 4÷7-8 ______________________________

ለ/ 4÷9 ______________________________

ሀ/ 6÷5-7 ______________________________

ለ/ 6÷8-9 ______________________________

ሀ/ 6÷10 ______________________________

ለ/ 6÷11 ______________________________

ለምንድነው ነህምያ መስራቱን ቀጥሎ የነበረው? ______________________________

______________________________

**ደረጃ ሰባት - ስራ**

ምኞት ትልቅ መነሳሻ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ስራ መከናወንን ያመጣል፡፡ ተግቶ መስራት ህልምን ተጨባጭ ያደርገዋል፡፡ ምንም አይነት ዕቅድ ይኑርህ ምኞትህ መፈፀም ያልቻለውን

ስራ ዕውን ያደርገዋል፡፡ መሰጠትና ጽናት የክርስቲያን ባህሪይ መለያ ናቸው፡፡ ውጤታማ መሪዎች ተሰፋ አይቆርጡም! ወድቀው ከመቅረት ይልቅ ለመጨረሻ ጊዜ የተነሱ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡

ከታች ባለው የነህምያ ቁርጠኝንት ባሻገር ህዝቡ መሰጠቱን እንዴት ነበር የገለፀው?
ነህምያ 4÷15-18

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

የስራቸው ውጤቶች ምን ነበሩ?

6÷15 ______________________________________________________

6÷16 ______________________________________________________

እግዚአብሔር እንድትሰራው የሚፈልገውን እየፈፀምክ ነው ያለኸው ወይስ መለወጥ መቀየር ትፈልጋለህ?

***አቅጣጫህን ካልቀየርክ፣ ወዳለምከው ስፍራ ትደርሳለህ፡፡***

መስጠትህንና ፅናትህን ለምትፈልገው ተግባር የሚሆን ለማሳደግ የሚከተሉት ያስፈለጉሃል፡፡
1. ግልፅ አላማ ለመከናወኑ በጋለ ፍላጐት የተደገፈ
2. በማያቋርጥ ተግባር የሚገለፅ ግልፅ ዕቅድ
3. ለሁሉም አሉታዊና ተስፋ አስቆራጭ ተፅዕኖዎች የፀኑ የተዘጋ አስተሳሰብ፡፡
4. ዕቅዶችህና ተግባርህ እንድትከተላቸው የሚያበረታቱህ አንድ ወይም ከዛ በላይ ከሆኑ ሰዎች ጋር የጓደኝነት ህብረት፡፡

ያንተንና የህይወት ቡድንህን የወደፊት ሁኔታ ስትመለከት፣ ወደፊት ለመሄድ መውሰድ ያለብህን ቀጣይ እርምጃ አክብብ፡፡

1. እግዚያአብሔርን ማመን
2. ምኞትና ህልም
3. ግቦች
4. ዕቅድ ማውጣት
5. ተግባር
6. እምነት/ፍቃድ/
7. ስራ

ከላይ ያከበብከውን ለመፈፀም ምን ማድረግ ያስፈልግሃል?

____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________

***«እንግዲህ ሥራ የሌለው እምነት በራሱ የሞተ ነው፡፡» (ያዕቆብ** 2÷17)*

# የሚመሩ መሪዎች
## ክፍል አራት

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው።

**የመሪነት ቡድኑን ከማገናኘትህ በፊት ቅድመዝግጅት፡-**

☐ 1. **መንፈሳዊ ዝግጅት ለደቀመዝሙር ማድረግ** የሚለው አንብብ

☐ 2. መንፈሳዊ ቤተሰብ ማሳደግ የሚለውን አንብብ ስዕላዊ መግለጫውን ለመግለፅና ለመወያየት ተዘጋጅ።

☐ 3. **ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደቶች** የሚለውን አንብብ። ሁሉም ጥያቄዎች እንዴት ከቤተክርስቲያኖችን ጋር እንደሚዛመድ መልስ ስጥ። ስዕላዊ መግለጫውን ለመሪነት ቡድኑ ለማብራራትና ለመግለፅ ተዘጋጅ።

☐ 4. **ወደ እድገት ማደግ ሂደት ነው** ለሚለው ክፍል የተዘጋጀውን የመቆጣጠሪያ ቅፅ ሙላ።

☐ 5. ከታች ያለውን ሪፖርት ሙላ

**ከመሪነት ቡድንህ ጋር በመሆን የሚከናወን።**

☐ 6. እግዚያአብሔር በዚህ ወር እንዴት በህይወት እንደሰራ አካፍል።

☐ 7. ከላይ ከ 1-5 ያሉትን ነጥቦች ከተወያየህ በኋላ ይህን ምልክት አድርግባቸው።

☐ 8. ባለፈው ወር ለራስህ ከያዝካቸው ግቦች አኳያ ምን እያከናወንክ አለህ?

☐ 9. ግቦችህን ለመፈፀም ምን ያስፈልግሃል? እኛስ ግቦችህን ትመታ ዘንድ የምናግዝህ ምንድን ነው?

**የህይወት ቡድንህ ሪፖርት**

☐ 10. __________ ሰዎች በመደበኛነት ይሳተፋሉ።

☐ 11. __________ አዳዲስ ተሳታፊዎች በዚህ ባሰልፍነው ወር ተካፍለዋል።

ስም ______________________________________________

አድራሻ ____________________________________________

☐ 12.በአንድ ለአንድ ስልጠና ላይ ያሉ

ዳይናሚክ መሰረታዊን ____________________ __________________ን ያሰለጥናል
____________________ ________________ን ያሰለጥናል

ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግን ____________________________________ን ያሰለጥናል

____________________ __________________ን ያሰለጥናል

ዳይናሚክ ማካፈልን ____________________ __________________ን ያሰለጥናል
____________________ __________________ን ያሰለጥናል

☐ 13. ________ ሰዎች በዚህ ወር በቡድናችን ውስጥ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል።

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 14.እርስ በእርስና ለቡድን አባላቶቻችሁ ፀልዩ።

☐ 15.ወደ ክፍል ሶስት የመልመጃ ዝግጅት አልፈህ ሂድ።

☐ 16.ለሚቀጥለው የሚመሩ መሪዎች ለሚለው ክፍለ ግዜ ቀን ___________________ ሰዓት ____________________ቦታ ___________________ መድብ

# ለደቀመዝሙር ማድርግ የሆነ መንፈሳዊ ዝግጅት

1. የተለወጠ ህይወት

*«ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው። አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፣ አዲስ ሆኖአል።»* (2 ቆሮንቶስ 5÷17)

አንድ ሰው ሰዎችን በመከታተል ስኬታማ ሊሆን ከፈለገ ክርስቶስን ማወቁ የግድ ነው። በእግዚያአብሔር ኃይል የተለወጠ ህይወት ለሌሎች ሊተርፍ ይችላል። በግል ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ ማወቁ ግድ ነው።

2. ንፁህ ህይወት

*«እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ከጠቀስኋቸው ነገሮች ቢያነጻ ለክቡር አገልግሎት የሚውል፣ የተቀደሰ፣ ለጌታው የሚጠቅም፣ ለመልካም ሥራም ሁሉ የተሰናዳ ዕቃ ይሆናል።»* (2 ጢሞቲዎስ 1÷21)

በጥሪታችን ላይ የእግዚያብሔርን ከፍተኛ በረከት ለማግኘት ከፈለግን፣ በውስጥና በውጪ ንፁህ መሆን ያስፈልገናል። የተሰወሩ ኃጢያቶች በሙሉ፣ በተለይ በሃሳብ የሚሰሩቱ በጌታ ኢየሱስ ቁጥጥር ስር ሊመጡ ይገባል። **ጥቃቅን ቀበሮዎች የወይኑን ስፍራ ያበላሹታል።** በህይወትህ ያለ ኃጢያት ከጊዜ በኋላ ቅንአትህ እንዲቀንስ ያደርጋል። ፍፁም እንድትሆን አይደለም የተፈለገው ነገር ግን በመታዘዝ አንድታድግ ነው።

3. የተማረከ ህይወት

*«እንግዲህ ወንድሞች ሆይ፤ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአበሔር ደስ የሚያሰኝ ሕያው መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሐር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ ፤ ይህም እንደ ባለ አእምሮ የምታቀርቡት አምልኮአችሁ ነው።»* (ሮሜ 12÷1)

ንፁህ መሆን አንድ ነገር ነው። ለጌታ መማረክ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ «ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው።» (ፊልጵስዩስ 1÷21) ። ለመከታተሉ ጉዳይ ለእግዚአብሔር ጥሪና ለፍቃዱ መሰጠት በጣም ትልቅ ነገር ነው። ወጣቱ ልጅ የራሱን አምስት እንጀራና ሁለት አሳ ለኢየሱስ አምጥቶ ነበር። ያለህን ሁሉ ወደ ክርስቶሰ አምጥተሃል።

4. ሸክም የሚሰማው ህይወት።

*«እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ፣ ሰው ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን፤»* (ቆላስያስ 1÷28-29)

ለሌሎች ሸክም መኖሩ በእርግጥ ይረዳል። ጵውሎስ ለራሱ ትውልድ የከበደ ልብ ነበረው። ሆኖም ከመጀመርህ በፊት ልበህ እስኪሰበር ድረስ መጠበቅ አይገባህም። የእኛ ግድ አለመሰኘት እያለ እግዚአብሔረ የራሱን ቃል ይባርካል። መጀመሪያ መሄድ አለበን ምክንያቱም መሄድ የእኛ ኃላፊነት ነው፤ እየሄድን እያለ፣ እግዚአብሔር ለሌሎች ዕድገት ሸክምን ያደርግብናል።

5. የሚራራ /ለሌሎች የሚያዝን/ ህይወት

*«ሕዝቡም እረኛ እንደሌለው በግ ተጨንቀውና ተመልካች የለሽ ሆነው ባየ ግዜ አዘነላቸው...ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።»* (ማቴዎስ 9÷36-38)

ብጫቂ ስለሆነ ሰዋዊ ፍቅር ወይም አድናቆት አይደለም እያወራን ያለነው፤ ከክርስቶስ ማንነት የተነሳ ከውስጥ ስለሚወጣ ንፁህ ፍቅር ነው እያወራን ያለነው፡፡ ሰዎች አንተ እንደምትወዳቸው እምነት ካደረባቸው አንተን ላይጠሉ ይችላሉ፡፡ /አይጠሉህም/ ሆኖም እስካለወደድካቸው ድረስ ደግሞ በጭራሽ አያምኑህም፡፡እንዴት ፍቅር ሰዎችን እንደሚስብ ማወቁ ያስገርማል፡፡ በእግዚአብሔር ፍቅር ብንሞላ ውጤቱ በማያቋርጥ ትጋት ሌሎችን ማገልገል ይሆናል፡፡ ፍቅርን እንዴት ልናገኝ እንችላለን? ከመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች አንዱ ፍቅር ነው፡፡ ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ያስፈልገናል፡፡

6. *ተንቀሳቃሽ ህይወት*

*«ደካሞችን እመስል ዘንድ፣ ከደካሞች ጋር እንደ ደካማ ሆንሁ፡፡ በሚቻለኝ ሁሉ አንዳንዶችን አድን ዘንድ ከሁላቸው ጋር ሁሉን ነገር ሆንሁ፡፡»* (1 ቆሮንቶስ 9÷22)

ቢሊይ ሰንደይ ብዙ ሰዎችን ወደ ጌታ ክርስቶስ ስላመጣበት ሚስጢር ተጠይቆ ነበር፡፡ እንዲህ አለ ይባላል ወደ መስኮቱ በመራመድ በውጪ በመንገድ ላይ ያሉትን ብዙ ሰዎች በመመልከት ኦ ወደ ሲኦል እየሄዱ ነው!ይል ነበር፡፡ ወንድሜ ይህ ዕውነት በልብህ ሲሞላ፣የሚጠፉትን እንድትታደግ ውስጥህን ያንቀሳቅሰዋል፡፡» የጠፉት ድነውና እንደገና ወደ እድገት መጥተው የማየት ፍላጐትህን አዳብር፡፡

7. *የሚፀና ህይወት*

*«በመካከላችሁ ሳለሁ ኢየሱስ ክርስቶስን ያውም የተሰቀለውን ፣ እርሱን ብቻ እንጂ ሌላ እንዳላውቅ ወስኜ ነበርና፡፡ »* (1 ቆሮንቶስ 2÷2)

ኃዋርያው ጵውሎስ እንዲህ አለ፣ «ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ»(ፊልጵስዩስ 3 ÷ 13) ደቀመዝሙር አድራጊ ለመሆን ወስኖ ነበር፡፡ በዚህ ጉዳይ ሃሳቡ ተይዞ ነበር፡፡

8. *የቃሉን አብርሆት ያገኘ ህይወት*

*«የቃልህ ትርጓሜ ያበራል ፤አላዋቂዎችንም አስተዋዩች ያደርጋል፡፡»* (*መዝሙር* 119÷130)

የእግዚአብሔር ቃል አንድን ሰው እንዴት ማደግ እንደሚችል ለመምራት የምንጠቀምበት መሆኑን ማወቁ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ያለ ቃሉ ሊያድግ አይችልም፡፡ በሮሜ 10÷17 ላይ እንዲህ ተብለናል፣ «እንግዲያስ እምነት የሚገኘው መልዕክቱን ከመስማት ነው፤ መልዕክቱም በክርስቶሰ ቃል ነው፡፡» (ሮሜ 10 ÷ 17) በሉቃስ 8 ÷ 11፣ በዘሪው ምሳሌ ውስጥ እንዲህ ተነግሮናል፣ «ዘር የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ነው፡፡»

9. *የሚፀልይ ህይወት*

*«ወደ እኔ ጩኸ፤ እኔም እመልስልሃለሁ፤አንተም የማታውቀውን ታላቅና የማይመረመር ነገር እገልጥልሃለሁ፤»* (ኤርሚያስ 33÷3)

እግዚአብሔር ፀሎትን ይመልሳል፡፡ ለደቀመዛሙርቶቻችንና ለእነርሱ ላለን አገልግሎት መፀለይ አለብን፡፡

# የሚያድግ መንፈሳዊ ቤተሰብ

ቡድናችንና ሌሎች ቡድኖች እያደጉና አዳዲስ ቡድኖችን እየወለዱ ሲስፋፉ፣ ቤተክርስቲያናችን ማህበረሰባችንን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መድረስ ትችላለች፡፡

ያ ተገቢ የሆነ ትጋት ነውን? ______________ አዎ ____________________ አይደለም

እንደዚህ ያለውን ስልት በእውነተኝነት ሞክር፣ የእኛ ላቅ ያለው ፍላጐት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?


________________________________________________________________________________

________________________________________________________________________________

የህይወት ቡድናችን በግል የሚታደግበት፣ አገልግሎት የሚጐለብትበት እና የመሪነት ብቃት መንፈሳዊ ቤተሰብ ሊሆን ይገባዋል፡፡

**መንፈሳዊ ቤተሰብ**

መንፈሳዊ እድገት በጥሩ ሁኔታ /በተሻለ ሁኔታ/ እንዲመጣ ከተፈለገ **መንፈሳዊ የቤተሰብ (ትንሽ ቡድን)** አውድ ወሳኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ይህም **የአንድ ለአንድ ክትትልና እንክብካቤ** ማድረግን ይጠይቃል፡፡




ሰዎች ትኩረታቸውን **ከራሳቸው** ፍላጐት ከሚሟላት ላይ አንስተው **የሌሎችን** ፍላጐት ለሚሟላት ትኩረታቸው ሲያደርጉ የዚያን ግዜ **የእድገት** ምልክትን አሳይተዋል ሊባል ይቻላል፡፡

## ቤተ-ክርስቲያን የተያያዘ መንፈሳዊ ቤተሰብ መሆን ይገባታል!


*ብዙ አብያተክርስቲያናት መንፈሳዊ ቤተሰብ ከመምሰል ይልቅ መንፈሳዊ እኅለማታ መስለዋል፡፡*

**መንፈሳዊ እኅለማታ** ____________________________________________ **ቤተሰባዊ እኅለማታ**

**ቤተክርስቲያናችን ትክክለኛ ቦታዋ ነው ብለህ በምትለው ቦታ የሀፐ ምልክት አድርግ ቤተክርስቲያን እንድትሆን የምትፈልገውን ቦታ ደግሞ ሀአ አድርግበት፡፡**

# ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት

በመንፈሳዊ ቤተሰብ ውስጥ ማደግ ከተፈለገ ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደትን ማጕልበት ወሳኝ ነው።




ስዕላዊ መግለጫውን በምታጠናበት ጊዜ የቀስቶቹን አቅጣጫ ልብ ብለህ ተመልከት

## የኢየሱስ ክርቶስን ወንጌል ለሌሎች በምናካፍልበት ግዜ ሂደቱ በእግዚአብሔር ዓላማ ይጀመራል።

ይህ ለቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ዓላማ ነው። እናም የእኛ ቀዳሚና ቀጣይ ግብ መሆን አለበት!

ለምን? ______________________________

ቤተክርስቲያን ሰዎችን ለመድረስና ለሌሎች ክርስቶስን ለማካፈል የቆመችበት የተወሰኑት ምክንያቶች የትኞቹ ናቸው? ______________________________

ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው የተቀበሉትን ሰዎች ምን ልናደርግላቸው አስበናል።

1. በወንጌል ከተደረሰ በኋላ **አዳዲስ ክርስቲያኖች መመገብ ያስፈልጋቸዋል?**
   **ፍቅርና እንክብካቤ በማድረግ ልንመግባቸው ይገባል።**

**በመሰረታዊ የክርስትና ትምህረት አዳዲስ ክርስቲያኖችን ስናሰለጥን፣**

***ሂደቱ ይቀጥላል***

ፀሎትና የመፅሀፍ ቅዱስ ጥናት መሰረታዊ ናቸው። ***አንድ አዲስ ክርስቲያን ሊገነዘባቸው የሚገቡ ሌሎች መሰረታዊ ነገሮች ምንድን ናቸው?*** ____________________________

______________________________________________________________________

_________________________________________________________________

አዳዲስ ሰዎችን በክርስትና መሰረታዊ ትምህርቶች ማሰልጠን ለምን አስፈለገ? _______

______________________________________________________________________

## 2. የሰለጠኑ ደቀመዛሙርት

***ምክንያቱም እራሳቸውን እንዲያባዙ ሆነው ስለሰለጠኑ፣***

## *ለማፍራት የታጠቁ ናቸው*

የሚያባዙ ከሰለጠኑ በኂላ የሚየሰለጥኑ ሰዎች ናቸው። አሁን ለመሪነት ብቁ ናቸው።

## 3.ሌሎችን የሚያሰለጥኑ ደቀመዝሙር አድራጊዎች *የመሪ መጎልበትና መተካት*

ሌሎችን በመሰረታዊ ትምህርቶች በማሰልጠን የሚያራቡ ደቀመዝሙር አድራጊዎች ናቸው።

## *አሁን እነዚህ የሚራቡ ደቀመዝሙር አድራጊዎች*

## *4.አገልግሎቱን የሚያስፋፉ መሪዎች*

### *ሲሆኑ፣ ሂደቱ እየተስፋፋ ይሄዳል።*

***ማስታወሻ፦ በእያንዳንዱ ሂደት ውስጥ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለሌሎች ማካፈል ዋና ትኩረት ነው!***

በአንድ እጅህ ስዕሉን በተራቁጥር 1 እና 4 ያሉትን ክቦች በመተው ሸፍን። ብዙ አብያተክርስቲያናት እየሰሩ ያሉት በ1 እና በ4 ውስጥ ያሉትን ብቻ ነው። አዳዲስ ሰዎችን በወንጌል እንደደረሱ ወዲያው ወደ አገልግሎት ያስገቧቸዋል። በ 2ኛውና 3ኛው ሂደት ውስጥ ሳያልፋ፣ ሰዎች በፍፁም ወደ መሪነት ሊሸጋገሩ አይችሉም። የአገልግሎት ክፍሎች ለደህንነታቸው እንኳን እርግጠኛ ባልሆኑ ሰዎች ይሞላሉ። ምናልባትም እንዴት በፀሎት ከጌታ ጋር መገናኘት እንደሚችሉ እንኳ ላያውቁ ይችላሉ። ምናልባትም በመንፈስ ቅዱስ ስለመሞላት ላያውቁ ይችላሉ፤ **ለሌሎች ወንጌሉን የማካፈሉም ነገር አጠራጣሪ ነው የሚሆነው!**

*አገልግሎታቸው ምን ያህል ውጤታማ ይሆናል ብለህ ታስባለህ?* ______________________

*ይህ የአንተን የቤተክርስቲያን ገፅታ ያሳያል?* ___________________-____________________

## ለታላቁ ተልዕኮ ዕውን መሆን ደቀመዝሙር የማድረግ ሂደት ወሳኝ ነው

# ወደ ብስለት ማደግ ሂደት ነው

በእድገት ሂደትህ ውስጥ ያከናወንካቸውን ተግባራት በዚህ (✓) ምልክት አድርግ።

☐ ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኜ አድርጌ ተቀብያለሁ።

☐ በሌሎች ክርስቲያኖች ክትትልን አግኝቼአለሁ።

☐ የሚከተሉትን የክርስትና ህይወት መሰረታዊ ትምህርቶች ተምሬአለሁ።

☐ ዳይናሚክ መሰረታዊ

☐ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ

☐ ዳይናሚክ ማካፈል።

☐ በመሰረታዊ የክርስትና ትምህርቶች እንደሰለጠነ ደቀመዝሙር ራሴን እቆጥራለሁ።

☐ ሌሎችን ለማፍራትና ለማሰልጠን ተዘጋጅቻለሁ።

☐ ሌሎችን በመሰረታዊ ትምህርቶች ለማሰልጠን ላይ ያለሁ ደቀመዝሙር አድራጊ ነኝ።

☐ ሌሎችን በመሰረታዊ የክርስትና ትምህርቶች እያሰለጠንኩ እገኛለሁ።

ስንት ግዜ እንዳሰለጠንክ በቁጥር አስቀምጥ።

__________ ዳይናሚክ መሰረታዊ

__________ ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግ

__________ ዳይናሚክ ማካፈል

☐ መሪነትን መማር - የተተኪ መሪ ስልጠናን አጠናቅቄአለሁ።

☐ ተተኪ መሪዎችን በ ☐ ዳይናሚክ ማካፈል - አሰልጥኛለሁ።

☐ መሪነትን መማር - የለማጅመሪ ስልጠና አሰልጥኛለሁ

☐ በሚከተሉት የአገልግሎት ዘርፎች የመሪነት ስልጠና ተካፍያለሁ።

______________________________________________

______________________________________________

☐ በሚከተሉት ቦታዎች በመሪነት ተቀምጬያለሁ።

______________________________________________

______________________________________________

☐ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ሁልግዜ እሰብካለሁ።

☐ ሌሎች ______________________________________

☐ የሚከተሉትን በማጠናቀቅ በዕድገት መቀጠል እፈልጋለሁ ____________________

______________________________________________

# የሚመሩ መሪዎች
## ክፍል አምስት

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው።

**የመሪነት ቡድኑን ከማገናኘትህ በፊት ቅድመዝግጅት፡-**

☐ 1. ቡድንህ እንዴት የራሳቸውን የህይወት ታሪክ ማካፈል እንዲችሉ ለማዘጋጀት የሚለውን ክፍል አጥና። ይህንን ወርክሾፕ በመጠቀም የራስህን የህይወት ታሪክ አዘጋጅ። ከመሪነት ቡድንህ ጋር እንዴት የራሳችሁን የህይወት ቡድን አባላት ለማስልጠን ዕቅድ ማድረግ እንደምትችሉ ለመወያየት ተዘጋጅ።

☐ 2. እንዴት አስደሳችና ውጤታማ የፍቅር ግብዣ ማዘጋጀት ይቻላል የሚለውን ክፍል አንብብ። ከመሪነት ቡድንህ ጋር በመሆን ግብዣ እንዴት ማድረግ እንደሚቻል ለማቀድ ለመወያየትና ለመከፋፈል ተዘጋጅ።

☐ 3. ከታች ያለውን ሪፖርት አጠናቅቅ።

**ከመሪነት ቡድንህ ጋር በመሆን የሚሞላ**

☐ 4. እያንዳንዱ ጌታ ያደረገለትንና የፀሎት ጥያቄውን ያካፍል። ስለ ቡድን አባላት አስፈላጊነት ተነጋገሩ።

☐ 5. ከላይ ከ 1-5 ያሉትን ነጥቦች ከተወያየህ በኋላ ምልክት አድርግ።

**በዚህ ወር የህይወት ቡድንህ ለመምራት የምትጠመድበት።**

☐ 6. የህይወት ቡድኔን አባላት የህይወት ታሪኬ የተሰኘውን ወርክሾፕ በመጠቀም ላሰለጥናቸው አቅጃለሁ። በሚከተለው ቀን ____________________ የወርክሾፕ ማሰልጠኛ መፅሀፍች ማዘጋጀት ያስፈልገኛል።

ከእኔ ጋር ፀልይ ____________________________________________

____________________________________________

☐ 7. የፍቅር ግብዣ ለማድረግ ምን አቅደሃል?

ዕቅድ____________________________________________

____________________________________________

**ስለህይወት ቡድንህ ዘገባ**

☐ 8. _______________ ሰዎች በመደበኛነት ይሳተፋሉ፡፡
☐ 9. _______________አዳዲስ ተሳታፊዎች በዚህ ባሰልፍነው ወር ተካፍለዋል፡፡

ስም ______________________________________________________________________

አድራሻ ____________________________________________________________________

☐ 10. በአንድ ለአንድ ስልጠና ላይ ያሉ

ዳይናሚክ መሰረታዊን ______________________ ___________________ን ያሰለጥናል
______________________ _________________ን ያሰለጥናል
ዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግን ________________________________________ን ያሰለጥናል
______________________ __________________ን ያሰለጥናል
ዳይናሚክ ማካፈልን ______________________ __________________ን ያሰለጥናል
______________________ __________________ን ያሰለጥናል

☐ 11. _________ ሰዎች በዚህ ወር በቡድናችን ውስጥ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል፡፡

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 12. እርስ በእርስና ለቡድን አባላቶቻችሁ ፀልዩ፡፡

☐ 13. ወደ ክፍል ስድስት የመልመጃ ዝግጅት አልፈህ ሂድ፡፡

☐ 14.ለሚቀጥለው የሚመሩ መሪዎች ለሚለው ክፍለግዜ ቀን_________________ ሰዓት ______________________ ቦታ _________________________ መድብ

# ቡድንህ የህይወት ታሪካቸውን እንዲያካፍሉ ለማዘጋጀት

- ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ወርክሾኘ በመጠቀም የህይወት ታሪክህን አዘጋጅ፡፡ (እንዴት ጌታን እንደተቀበልክ የግል ምስክርነት)
- ለህይወት ቡድንህ የህይወት ታሪክህን አካፍል፡፡
- ለእያንዳንዱ የቡድኑ አባል የህይወት ታሪኬ - ወረክሾኘ ፅሁፍ እንዲደርሳቸው አድርግ፡፡ (ማስታወሻ፡- እነዚህን ማስታወሻዎች ልትገለብጥ ትችላለህ ይህ ወርክሾኘ በዳይናሚክ ደቀመዝሙር የማድረግ ትምህርት 8 እና በዳይናሚክ ማካፈል ትምህርት 1 ውስጥ ይገኛል፡፡) እያንዳንዱ ሰው መመሪያውን እንዲያነብና በሚቀጥለው ሳምንት ከመምጣታቸው በፊት ለ 1 ደቂቃ ምስክርነታቸው እንዲዘጋጁ ምራቸው፡፡
- በሚቀጥለው የህይወት ቡድን ስብሰባ ላይ በጥንድ እንዲሆኑ አድርጋቸው፡፡ (ወንድ ከወንድ ወይም ሴት ከሴት ጋር) የፃፉትን ሊያካፍሉ ይገባቸዋል፡፡ እርስ በእርሳቸው ምስክርነታቸውን ያሻሽሉና ግልፅ ያደርጉ ዘንድ መረዳዳት ይችላሉ፡፡
- ቡድኑ የያዛቸውን በርካታ ምስክርነቶች ከቡድንህ ጋር ተካፈል፡፡
- ምስክርነታቸውን የሚያካፍሉትን ማበረታታትህንና ቃላት በጠራቸው ግዜ ማገዝህን አትርሳ፡፡
- እያንዳንዱ ምስክርነቱን ካካፈለ በኋላ ቡድንህን የቀድሞ ታሪክ እንዴት ጌታን እንዳገኙና ጌታን ካገኙ በኋላ ያለው ህይወታቸው ምን እንደሚመስል ጠይቅ፡፡
- መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ላይ በዝግታ ጠቁማቸው፡፡ ማንንም እንዳታሳፍር በጣም ተጠንቀቅ፡፡
- ይህ እግዚአብሔር በእነርሱ ያሳየበት የአስደናቂው ፀጋው ምስክርነት መሆኑን እየነገርክ አበረታታቸው፡፡ ሁልግዜ ሊያካፍሉትም ይገባቸዋል፡፡ የህይወት ታሪካቸው ወንጌል ባይሆንም ወንጌልን ለመግለጫና ወንጌሉን እንዲያካፍሉ ሊመራቸው ይችላል፡፡
- «እግዚአብሔርን በግልህ ልታውቀው ትወዳለህ?» ወይም «አራቱ መንፈሳዊ ህጎች» የተሰኙትን ለመመስከሪያ የሚረዱ ትንንሽ መፅሀፍቶች ለሰዎች በመስጠት ወንጌሉን እንዲመሰክሩ አበረታታቸው፡፡

# የህይወት ታሪኬ ወርክሾኘ

የዚህ ወርከሻኘ አላማ የህይወት ታሪክህን በመጻፍ ለሌሎች እንድታቀርብ እንድትችል መርዳት ነው።

## እንዴት የህይወት ታሪኬን ወይም የግል ምስክርነቴን ላዘጋጅ እችላለሁ?

ማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ በጥንቃቄ ከተቀነባበረ በጣም ውጤታማ በሆነ መልኩ ሊቀርብ ይችላል። በጥንቃቄ የተቀነባበረ ምስክርነት፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የታገዘ ለሁሉም የምስክርነት ጊዜ ሊሆን ይችላል አፋጣኝና ውጤታማ ጥቅም ይሰጣል። የሚሰሙት ሁሉ እርሱን ያውቁት ዘንድና ክርስቶስን በግል መቀበል ምን መሆኑን ያውቁ ዘንድ፣ ክርስቶስን እንደዚህ ባለው ግልፅ፣ ማራኪ ነገር ግን ቀላል በሆነ መንገድ ማቅረብ ምኞታችን ሊሆን ይገባል።

**የግል ምስክርነት አድርግና አታድርግ**

**አድርግ**

1. በምትፅፍበት ጊዜ እግዚአብሔር ምሪት እንዲሰጥህ ፀልይ (ያዕቆብ 1÷5-6)
2. የአራት ነጥብ ቅደም ተከተል የህይወቴ ታሪክ (የመስሪያ ወረቀቱን ናሙና ተመልከት)
   ሀ/ ክርስቶስን ከማወቅህ /ወደክርስቶስ ከመምጣትህ/ በፊት ስለነበረህ ህይወት አካፍል።
   ለ/ እንዴት ወደ ክርስቶስ እንደመጣህ አካፍል። (ለይተህ ተናገር)
   ሐ/ክርስቶስን ከተቀበልክ በኂላ ስላለው ህይወትህ ተናገር። (በህይወትህ የመጣውን አዎንታዊ ለውጥና እርሱ ለአንተ ምን ማለት እንደሆነ)
   መ/ ተስማሚ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ ስጥ።
3. ከልጅነትህ ጀምረህ ክርስቲያን ከሆንክ ነጥበ "ሐ"ን አጥብቀህ ተናገር።
4. ለነጥብ (ሀ) 10 ደቂቃ ያህል ተጠቀም፣ ለነጥብ (ለ) 2 ደቂቃ፣ ለነጥብ (ሐ) 25 ደቂቃ እና ለነጥብ (መ) 5 ደቂቃ ተጠቀም፤ ነጥብ (ሀ) እና (ለ) ያለፉ ታሪኮች ናቸው። አንዴ ካዘጋጀሃቸው በኂላ መለወጥ ላያስፈልግህ ይሆናል። ነጥብ (ሐ) ክርስቶስ አሁን በህይወትህ እያደረገው ስላለው ስለሆነ ወቅታዊና ትኩስ ሆነው መቀመጥ ይኖርባቸዋል።
5. በጣም በሚማርክና ቀልብን በሚስብ ዐ.ነገር ጀምረህ በጥሩ መደምደሚያ ጨርስ። ምስክርነቱ እስከሚያልቅ ድረስ /በሁሉም ሰዓት/ አንድን ርዕስ ጉዳይ ተከተል ምሳሌዎች፡-

   የመኖር ዓላማ
   የአንድ አካል አባል የመሆን ስሜት
   የእግዚአብሔር ቃል
   የደህንነት ማረጋገጫ
   ከሞት ፍርሀት ነፃ መውጣት
   የአምሮ ሰላም
   ፍፃሜ
   የእግዚአብሔር ፍቅር
   የእግዚአብሔር ይቅርታ
   ስኬት
6. ሌሎች ከአንተ ያለፈ ወይም የአሁን ልምምዶችህ ውስጥ አብረውህ እንዲሆኑ እንዲሰማቸው አድርገህ ፃፈው። ስለአመለካከት ለውጦችህ አውራ እነርሱም ከጥላቻ ወደ ፍቅር፣ ከጭንቀት ወደ ደስታ፣ ከስጋት ወደ ሰላም ካለመታገስ ወደ መታገስ ከስርዓት አልበኝነ ወደ ሰላማዊ ሰውነት እንደመጣህ
7. ከመጨረሻው ረቂቅ በፊት በጥንቃቄ አርመው፤ እንደ አስፈላጊነቱም ደግመህ ፃፍ።
8. ምስክርነትህን በማስታወስና፣ በመለማመድ ከአንተ ጋር እስኪዋሃድ ድረስ በአዕምሮህ ያዘው።

**አታድርግ**

1. የሚከቡዱ ክርስቲያናዊ ቃላቶችን አትጠቀም - እነዚህነ የመሳሰሉ ቃላትን፡- መዳን፣ መለወጥ፣ መወቀስ፣ ዳግሞ መወለድንና ኃጥያት፤ ምንም እንኳ እነዚህ ቃላቶችና ሐረጉች ለእኛ ውድ ቢሆኑም፣ ብዙውን ጊዜ ክርስቲያን ያልሆኑ ሰዎች አይረዷቸውም።
2. በብዙ ቃላቶች አትዘብዝብ፤ ማለት የፈለከውን ብቻ ተናገር ወይም እንዴት መጥፎ ህይወት እንደነበረህ አጠንክረህ ተናገር።

3. እነዚህን የመሳሰሉ ቃላቶችን አትጠቀም። የሚያስደንቅ፣ የተከበረ፣ ዕፁብ ድንቅ ወ.ዘ.ተ
4. ቤተ እምነቶችን አትግለፅ፣ በተለይም እነርሱን በሚያንቋሽሽ መልኩ
5. ስለማንኛውም ግለሰብና ቡድን በመጥፎ አትናገር።
6. የክርስትና ህይወት ምንም ዓይነት ችግር እንደሌለበት አድርገህ በመናገር በሰዎች ላይ ተፅዕኖ አታድርግ።

## የህይወት ታሪክህን ገምግም

1. የምናገርበት ጭብጥ መልዕክት ምንድን ነው? ________________________________
2. የመክፈቻዬ ዐ.ነገር የሰዎች ቀልብ ይይዛል ? ________________________________

**ክርስቶስን ከመቀበሌ በፊት ያለው ህይወቴ**
1. ክርስቲያን ላልሆነ ሰው እንደምናገር ማስታወሴ ይረዳኝ ይሆን? ንግግሬ ከእውነት ያልራቀ ነው?
2. ክርስቶስ እንደሚያስፈልገኝ ለማረጋገጥ ያገዘኝ ነገር ምን ነበር?

**እንዴት ክርስቶስን እንደተቀበልኩ**
1. እንዴት በእርግጥ ክርስቶስን ወደ ህይወቴ እንዳስገባሁት ለይቼ በመግለፅ ተናግሬ ነበር?
2. ምስክርነቴን ከመስማቱ የተነሳ ክርስቶስን መቀበል እንዴት እንደሆነና ምን ማለት እንደሆነ ሊያውቅ ይችላል?

**ክርስቶስን ከተቀበልኩ በኋላ ያለው ህይወቴ**
1. ክርስቶስ ህይወቴን እየቀየረው እንዳለ ስናገር ቀላልና ግልፅ ምሳሌዎችን ተጠቅሜ ነበር?
2. ንግግሬ ትክክል ነበር? ማንም ፍፁም እንዳልሆነ ማስታወስ።
3. በህይወቴ ልዩነትን ያመጣው ክርስቶስ እንደሆነ ያሳያል?

**ተስማሚ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ**
1. ይህ ጥቀስ ከህይወት ታሪኬ ጭብጥ መልዕክት ጋር ይያያዛል?

**ምስክርነትህን ስታካፍል እርግጠኛ መሆን ያለብህ ጉዳይ**
1. በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና፣ በፍቅርና በታላቅ ፍላጐት አካፍለው (ኤፌሶን 5÷18)
2. በተፈጥሮህና ዘና ባለ የድምፅ ቃና በግልፅ ተናገር።
3. በምትናገርበት ጊዜ አጉል ልማዶችን ማለትም አፍንጫን መነካካት፣ ጉሮሮን መጥረግና ፀጉርህን ማከክ ወ.ዘ.ተ አስወግድ።
4. ለክርስቶስ ሰዎች እንዲወስኑ ማስገደድን አስወግድ። አስታውስ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ነው የሚወለዱት በአሳማኝ ንግግሮችና በሰዎች አስተሳሰብ አይደለም፤ ምንም እንኳ እግዚአብሔር ሁለቱንም ሊጠቀም ቢችል።
5. ሰዎችን መስበክ አስወግድ። በስብከት መልክ ሳይሆን በምስክርነት መልክ አቅርበው። "እኔ" እንጂ እናንተ ወይም አንተ አትበል። አስታውስ ታሪኩ ያንተ ነው።
6. ብዙ ጊዜ ፈገግ በል! ጌታ ደስተኛና የሚያበራ ፊት እንዲሰጥህ ፀልይ።

# የህይወቴ ታሪኬ የመስሪያ ቅፅ

**ክርስቶስን ከመቀበሌ በፊት ያለው ህይወቴ፡-**

**እንዴት ክርስቶስን እንደተቀበልኩ፡-**

**ክርስቶስን ከተቀበልኩ በኂላ ያለው ህይወቴ፡-**

**ተስማሚ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ፡-**

# ከህይወት ቡድንህ ወይም አብረውህ ከሚሰሩ በርካታ ቡድኖች ጋር እንዴት አስደሳችና ውጤታማ የአንድነት ጊዜ ማድረግ እንደሚቻል

### የአብሮነት ግዜ ምንድነው?

በየሳምንቱ እየተገናኘን በእግዚአብሔር ቃል አስደናቂ እውነቶች እየተባረክን ነው፡፡ ከእግዜአብሔር ጋር አብሮ መሄድና እርስ በእርስ ህብረት ማድረግ ምንኛ በረከት ነው፡፡ ህይወታቸውን የነካናቸው ብዙ ሰዎች ስለእንደዚህ አይነቱ ህብረት ምንም የሚያውቁት ነገር የለም፡፡ በአብሮነት ጊዜው ላይ እንዲገኙ በመጋበዝ ደስታችንን የማካፈል እድሉ አለን፡፡ ክርስቲያናዊ ህብረትን ሊለማማዱና እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ማድረግ እንደሚችሉ ግንዛቤን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

### ማንን ልጋብዝ?

የፈለከውን ማንኛውንም ሰው መጋበዝ ትችላለህ፤ ነገር ግን በተለይ እየፀለይክላቸው ያለሃቸውን ሰዎች ብትጋብዝ ጥሩ ነው፡፡ በተፅዕኖ ክልልህ ቅፅ ላይ የምታውቃቸው ሰባት ሰዎችን ለምን የመጥሪያ ወረቀት አዘጋጅተህ እንዲመጡ አትጠይቃቸውም፡፡ የምትሰበሰቡበት ክፍል መያዝ የሚችለውን ያህል እስከሚይዝ ድረስ ጋብዝ፡፡

### ምን ብዬ ሰውን ልጋብዝ?

ጓደኞችህ የአብሮነት ጊዜ እንደሚያደርጉና በእዛ ኘሮግራም ላይ አንድ ሰው አምጣ እንደተባልክ ልትነግራቸው ትችላለህ፡፡ አንድ ሰው እንዴት የክርስትና ዕውነተኝነትን በዚህ አለም ውስጥ እንደደረሰበት የሚገልፅውን የህይወት ተሞክሮ እንደሚያካፍል ገልፀህ ለመናገርህ እርግጠኛ ሁን፡፡ በኘሮራሙ ላይ ስለመገኘታቸው ላስብበት ካሉህ፣ ለመልሳቸው መልሰህ አንተው ራስህ እንደምታገኛቸው ግለፅላቸው፡፡ የአበሮነት ጊዜውን ቀን ፣ ሰዓት፣ ቦታና ይዘቱን ንገራቸው፡፡ እንደምትጠራቸውና አብረሃቸው ይዘሃቸው እንደምትሄድ ፍቃደኝነትህን አሳያቸው፡፡ ለመምጣት ለወሰኑት (ግለሰቦች ወይም ቡድኖች) ስማቸውን እየለየህ ፀልይላቸው፡፡ አንዴ ለመምጣት ከወሰኑ በኂላ፣ ምንም አይነት ነገር ከመምጣት እንዳያግዳቸው ፀልይ፡፡

### በአብሮነት ጊዜ ኘሮግራም ላይ ምንድን ነው የምናደርገው?

እያንዳንዱ ቡድን የራሱን የአብሮነት ጊዜ ያቅዳል፡፡ ለግንዛቤህ ጥቂት ሃሳቦችን ለመሰንዘር ያህል

- የጠረጴዛ ጨዋታዎች
- ሽርሽር
- በመናፈሻ ውስጥ የሚከናወኑ የስፖርት እንቅስቃሴዎች

### የሚደገፍ አጀንዳ

- እንግዶች እንደደረሱ በሰላምታ ተቀበላቸውና ስማቸው የሰፈረበት ደረት ላይ የሚለጠፍ ወይም የሚታሰረውን ምልክት ስጣቸው፡፡
- ምናልባት እርስ በእርሳቸው በሚተዋወቁበት ጨዋታ ወይም ጥያቄዎች እንግዶቹ ሁሉ ከደረሱ በኂላ መጀመር ትችላለህ፡፡
- ክንውኖቹን መጀመር፤ የጠረጴዛ ጨዋታዎች፣ ካንፋየር ወይም ሌሎች ክንውኖች
- የክርስቲያናዊነት እውነታ በዚህ አለም በተሰኘው ርዕስ ምስክርነት ማካፈል፡፡ (ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 1-3 አማራጮች በአንዱ መልክ ማቀረብ)
- መከታተል፡፡

## የክርስቲያናዊነት እውነታ በዚህ አለም ውስጥ ለማካፈል፡-

**አማራጭ 1፡- ሰዎች ቡድናችንን ተቀላቅለው ስለ እግዚአብሔር እንዲማሩ መጋበዝ**

- ለእያንዳንዱ የአስተያየት መስጫ ካርዱን ማደል። በምሽቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት መጠየቅ። በተለይ በቡድናችን ላይ እንዲገኙ የሚፈልጉ ከሆኑ ካርዱን ምልክት አድርገው በሳጥን ውስጥ እንዲያስቀምጡ ጠይቃቸው።
- በመደበኛ ሁኔታ በቡድንህ መካፈል እንደሚችሉ ንገራቸው። ቀኑን፣ ሰዓቱንና ቦታውን ግልፅ አድርግላቸው። እንግዶችን ያመጡትን ሰዎች በሚቀጥለው የህይወት ቡድን ፕሮግራም ላይ ይዘዋቸው እንዲመጡ አበረታታቸው።
- ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ ለመርዳት ሁልግዜ ከአጠገባቸው መሆን እንደምንፈልግ ንገሯቸው።
- ካርዶቹን ገልብጠው ቅርጫት ውስጥ እንዲያስቀምጡ ንገራቸው።
  (ማሳሰቢያ፡- እንግዶቹ ሳይሄዱ ካርዶቹን እንዳታነብ)
- በኩኪስና በቡና ራሳቸውን እንዲያዝናኑ ጋብዛቸው።

**አማራጭ 2፡- የወንጌል ማቅረቢያ ፎርም**

- ***እግዚአብሔርን በግልፅ ልታውቀው ትፈልጋለህ?*** *የሚለውን ትንንሾቹን የወንጌል መመስከሪያ መፅሀፍት በመጠቀም ቡድኑን በአንድነት ሰብስብ እና መሪው ወንጌል ወደማቅረቡ ሊሸጋገር ይገባዋል። እንዲህ ማለት ይችላል።* ***በዛሬው ምሽት እዚህ በመገኘታችን ደስ ብሎናል መልካም ግዜ በአንድነት አሳልፈናል። በትንሹ ቡድናችን እንዴት ትርጉም ያለው ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን እንደሚችል እየተማርን አለን። አሁን የእምነታችን ዋና ፍሬ ነገርና እንዴት ያንኑ አይነት ግንኙነት ማግኘት እንደምትችሉ ላካፍላችሁ እወዳለሁ።*** እያንዳንዱ ሰው እያንዳንዱን ክርስቲያን ጨምሮ የመመስከሪያ ትንሿን መፅሀፍ እስከመጨረሻው ያለምንም ተጨማሪ ማብራሪያ ስታነብ እንዲከታተሉህ አበረታታቸው።
  የንስሀ ፀሎት ክፍሉን በሙሉ ካነበብክ በኋላ ክርስቶስን ለመቀበል ፍቃደኛ የሆኑትን ሰዎች እንደገና የንስሃ ፀሎቱን በምታነብበት ጊዜ እንዲከተሉህ ጋብዛቸው። በአንድ ጊዜ አንድ ሐረግ ብቻ እንዲደግሙ አድርግ።
- እያንዳንዱን ክርስትያን ጨምሮ ለእያንዳንዱ ሰው የአስተያየት መስጫ ካርዱን አድላቸው። ስለ ምሽቱ ያላቸውን አስተያየት እንዲሰጡ ጠይቃቸው፤ ለእነርሱ አግባብነት ያለውን ሳጥን ምልክት እንዲያደርጉ፤ በተለይም ክርስቶስን ለመቀበል የንስሀ ፀሎት ከፀለዩ ወይም በቡድናችን ለመካፈል (ለመሳተፍ) ከፈለጉ።
- በመደበኛ ሁኔታ በቡድንህ መካፈል እንደሚችሉ ንገራቸው። ቀኑን፣ ሰዓቱንና ቦታውን ግልፅ አድርግላቸው። እንግዶቹን ያመጡትን ሰዎች በሚቀጥለው የህይወት ቡድን ፕሮግራም ላይ ይዘዋቸው እንዲመጡ አበረታታቸው።
- ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ ለመርዳት ሁልግዜ ከአጠገባቸው መሆን እንደምንፈልግ ንገራቸው።
- ካርዶቹን ገልብጠው ቅርጫት ውስጥ እንዲያስቀምጡ ንገራቸው።
  (ማሳሰቢያ፡- እንግዶቹ ሳይሄዱ ካርዶቹን እንዳታነብ)
- በኩኪስና በቡና ራሳቸውን እንዲያዝናኑ ጋብዛቸው።

**አማራጭ 3 ፡- የግል ምስክርነትና የወንጌል ስብከት**

- እንዴት ትርጉም ያለው ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር እንዳሳደገ የሚካፍለውን ግለሰብ አስተዋውቅ። የግለሰቡ(የጥንዶች) ምስክርነት በደንብ የተዘጋጀና 10 ደቂቃ ብቻ የሚወስድ መሆን ይኖርበታል።
- ከምስክርነቱ መጨረሻ እነርሱ ወይም ሌላ ሰው ወደ ወንጌል ስብከቱ ያሸጋግራቸው፤ **«እግዚአብሔር በግልህ ማወቅ ትፈልጋህ?»** በሚለው ርዕስ የተዘጋጀውን ትንሽ የወንጌል መመስከሪያ መፅሀፍ በመጠቀም ወደ ሚቀርበው የወንጌል ስርጭት ጊዜ መስካሪዎቹ ከምስክርነቱ ወደ ትንሿ የወንጌል መመስከሪያ መፅሀፍ እንዲህ በማለት ሊሸጋገሩ ይችላሉ፣ «***እኔ /እኛ እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር***

*ወዳለን የግል ግንኙነት ልምምድ እንደመጣን ስናካፍላችሁ ነበር። አሁን ደግሞ እንዴት እንደዚህ ያለ ዕድል ሊኖራቹሁ እንደሚችል ልናካፍላችሁ እንወዳለን።»* እስከ ገፅ 10 መጨረሻ ያለውን የወንጌል መመስከሪያ ያለ ምንም ማብራሪያ ስታነብ፣ እያንዳንዳቸው (**ክርስቲያኖቹንም ጨምሮ**) እየተከታተሉህ እንዳለና የወንጌል መመስከሪያውን እንደያዙ አረጋግጥ።

ጸሎቱን አንብበህ እንደጨረስክ ክርስቶስን ለመቀበል ፍቃደኛ ጸሎቱን ደግመህ በማንበብ አብረውህ እንዲጸዩ ጋብዛቸው።

- የሐሳብ መስጫ ካርዶቹን ለእያንዳንዳቸው አድል (**ክርስቲያኖቹንም ጨምሮ**) ስለምሽቱ ያላቸውን አስተያየት ጠይቃቸው።እነርሱን የሚመለከት ማንኘውንም የትያቄ ሳጥን ላ ምልክት እንዲያርጉ ጠይቃቸውአ፣ በተለይ ክርስቶስን የተቀበሉ ከሆነና በህብረቱ ተካፋይ ለመሆን ከፈለጉ።
- በመደበኛ ሁኔታ በቡድንህ መካፈል እንደሚችሉ ንገራቸው። ቀኑን፣ ሰዓቱንና ቦታውን ግልፅ አድርግላቸው። እንግዶቹን ያመጡትን ሰዎች በሚቀጥለው የህይወት ቡድን ኘሮግራም ላይ ይዘዋቸው እንዲመጡ አበረታታቸው።
- ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት እንዲያድጉ ለመርዳት ሁልግዜ ከአጠገባቸው መሆን እንደምንፈልግ ንገራቸው።
- ካርዶቹን ገልብጠው ቅርጫት ውስጥ እንዲያስቀምጡ ንገራቸው።
  (ማሳሰቢያ፡- እንግዶቹ ሳይሄዱ ካርዶቹን እንዳታነብ)
- በኩኪስና በቡና ራሳቸውን እንዲያዝናኑ ጋብዛቸው።

## ክትትል

- የቡድን መሪዎች፣ ክርስቶስን የተቀበሉ ሰዎችን ልታነኙዋቸውና በቡድናችሁ ካለ አንድ ሰው ጋር በማጣመድ የዳይናሚክ መሰረታዊን 4 ክፍለጊዜዎች እንዲካፈሉ ማድረግ ይኖርባችኋል።

ይህ እምነትን የሚያነሳሳ ልምምድ ነው። እግዚአብሔር እምነትህን ያከብራል!

*ምንም አይነት ጥያቄ ወይም የሚያስፈልግህ እርዳታ ካለህ መጋቢህን ወይም አሰልጣኝህን አግኘው።*

## አስተያየትና መመሪያ ለእንግዳ ተቀባዩ

እያንዳንዱ ጥንድ አለምን በአያሌው ለመለወጥ ትንሽ እገዛ ማድረግ ይችላል።

1. የቡድንኑ ሦስት ጊዜ የሚያህል ሰዎችና በክፍሉ ሳይጨናነቁ እስኪቀመጡ ድረስ ሰዎችን ጋብዝ።
2. ከሁሉም ከምታውቃቸው አካባቢ ሰዎችን ጋብዝ

ሀ/ የጐረቤት ጓደኞች

ለ/ የክለብ አባላቶች

ሐ/ በሙያና በስራ የምታውቋቸው።

3. ረዳት እንግዳ ተቀባዩች ለእንግዶች አቀባበል፣ ለዝግጅቶችና ለአገልግሎት ዋና አስተናጋጆችን ይረዱ ዘንድ አዘጋጅ።
4. ማራኪ ጥሪ አድረግ።

ሀ/ ዝግጅቱ ሊከናወን 10-14 ቀናት አካባቢ ሲቀረው በቀድሚያ የጥሪ ካርዱ እንዲደርሳቸው አድርግ

ለ/ ከቀን ፣ ሰዓት፣ቦታ የመልዕክቱ ጭብጥ መልዕከት ወ.ዘ.ተ ባሻገር የሚከተለውን ያካተተ ይሁን።

***እሸቱና መቅደስ «የክርስትና ዕውነታ በዚህ ዓለም ውስጥ» በሚል ርዕስ አጭር መልዕክት ያደርጋሉ።***

5. በስልክ የጥሪው ካርድ ለተጋባዦች እንደደረሰ ተከታተል።
6. እንግዶቹ እንደደረሱ በመቀበል ዘና እንዲሉ አገልግላቸው
7. ስማቸውን የያዘውን በደረታቸው የሚለጠፍ ወይም የሚታሰረውን ትንሽ ካርድ ስጣቸው።
8. ለስለስ ያለ በሙዚቃ መሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ የእራት ላይ ሙዚቃ ክፈትላቸው። (መንፈሳዊ አይሁን)
9. መንፈሳዊ ባልሆኑ ጉዳዮች (ስፖርቶች፣ ፋሽኖች ትምህርት ቤት፣ ቤተሰበ፣ ወ.ዘ.ተ) እንዲጨዋወቱ አበረታታቸው።

10. አማኝ ያልሆኑት ሰዎች ባይተዋር ሊያደርግ ስለሚችል የቤተክርስቲያን ወይም መንፈሳዊ ጨዋታዎችን አስወግድ፡፡
11. የሲጋራ መተርኮሻ አቅርብ
12. ክርስቲያን ያልሆኑ ጓደኞቻቸውን ይዘው እንዲመጡ ዕድሉን የሰጠሃቸውን ክርስቲያኖች አበረታታ፡፡
13. በወንዶችና በሴቶች መካከል መለያየት ለማስወገድ ክርስቲያን ወገኖችን እንዲዘዋወሩ ጠይቃቸው፡፡
14. ቀለል ያሉ ምግቦችን ተናግረው ከጨረሱ በኋላ እንደገና በማቅረብ ቀጥታ ወደ ዘና ያለ ሁኔታ መግባት፡፡

## የአንድነት ግዜው ይዘት

1. እንግዶቹ እንደደረሱ ቀለል ያሉ ምግቦችንና መጠጦችን ማስተናገድ
   ሀ/ ስማቸው የተፃፍትንና በደረት ላይ የሚውለውን ምልክት ስጣቸው፡፡
   ለ/ ሰዎች ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ አድርግ!
   ሐ/ ጭውውቶች መንፈሳዊ ባልሆኑ ርዕሰ ጉዳዩች እነዲሆኑ ማድረግ
2. ወደ መደበኛ የምሽት ጊዜ ጨዋታዎች መሄድ (ወይም ወደታቀደው ማንኛውም ክንውን - በግምት ከ ለ1-1/2 ሰዓት)
3. የምግብ አገልግሎትን ማድረግ (ሰዎች እንዲዘዋወሩ ስለሚረዳ በብፌ መልክ ቢቀረብ ጥሩ ይሆናል፡፡ ለ45 ደቂቃ ያክል)
4. ጥንዶቹ አጭር ንግግር ያድርጉ ( የ30 ደቂቃ የሚወስድ የምስክርነታቸው ጊዜ የትንሿ የወንጌል መመስከር መፅሀፍ)
5. ተጨማሪ ሻይ ቡናና እና ጣፋጭ እንደጨረሱ ማቅረብ፡፡
   በዚህ ጊዜ እንግዳ ተቀባዩችና ተናጋሪዎች ሰዎች ዘና ባለ ሁኔታ እንዲሆኑ ይረዷቸው፡፡
   ይህ ይዘት አንተ ከግብህ እንዳትወጣ ሆኖ የተዘጋጀ ነው፡፡

## ለአንድነት ግዜው የሚያስፈልጉህ ነገሮች

______ የጥሪ ካርዶች
______ ሰፋፊ ጉርንዳ ሳህኖች
______ ብርጭቆዎች ወይም የፕላስቲክ መጠጫዎች
______ የምግብ ማቀረቢያ ሳህኖች ፣
የሻይና ቡና መጠጪያዎች ወ.ዘ.ተ
______ ዝርግ ሣህኖች
______ ምግቦችና መጠጦች ልብስን እንዳይነኩ
የመከላከያ ጨርቆች
______ የሲጋራ መተርኮሻ
______ ሻማና የሻማ ማስቀመጫ
______ የሀሳብ መስጫ ካርድ
______ ትንንሽ የወንጌል መመስከሪያ መፅሀፍቶች፡፡

**የምግብ አይነቶች ዝርዝር**

______
______
______
______
______

**የምግብ መስሪያዎች**

______
______
______
______
______

# ለክርስቲያን ወገኖቻችን የሚሆን ትንሽ ጉርሻ

ምናልባት ክርስቲያን ያልሆነ ጓደኛ፣ ዘመድ፣ ጐረቤት፣ የክበብ አባል ወይም በስራ የምትገናኘው ሰው ቢኖርህና ከርሱም ጋር ከአንተ ጋር የጨዋታ፣ የምግብና አብሮህ የክርስትናን እውነታ እስኪሰማ ድረስ የወዳጅነት ግንኙነት የምትፈልግ

**ከሆነ**

ለምን ያንን የወዳጅነት ግንኙነት አሁን አትጀምረውም

1. ለእራት ጋብዛቸው። (መንፈሳዊ ባልሆኑ ርዕስ ጉዳዩች እንደ ስፖርቶች ፋሽኖች፣ በትርፍ ጊዜ የሚሰሩ ስራዎች (እንደዝንባሌ)፣ የትምህርት ቤትና የአካባቢ ጉዳዩች ወ.ዘ.ተ ማንሳትና መጫወት)

**በመቀጠል**

2. ወደሚወዱት የስፖርት ጨዋታዎችን መጋበዝ

**ወይም**

3. በትርፍ ጊዜ እንደዝንባሌ በሚሰሩ ስራ ወይም በልጆቻቸው ፍላጐትህን አሳይ = ቤተኝነት እስኪሰማቸው ድረስ

**እነኚህ ነገሮች ፍቅርህን የሚያሳዩና በሚቀጥለው ግንኙነት በር ይከፍታሉ፤**

ማለትም ከላይ በአብሮነት ጊዜህ ላይ ለምታደርገው ጥሪ በር ይከፍታል። እንደ ጓደኛቸው ሆነህ ወንጌሉን ለእነርሱ ልታካፍል ትችላለህ።

**ክርስቲያን ያልሆኑ ጓደኞችን ስንጠራ ልንከተላቸው የሚገቡ ሐሳቦች**

1. በግል በፅሁፍ የሆነ ጥሪ አቅርብ።
2. እንደዚህ ብለህ ልትፅፍ ትችላለህ፣ ***«የእኛ ጓደኞች የአብሮነት ግዜ አዘጋጅተዋል (የወንጌል ስርጭት ግዜ አይደለም)። ምን እንደሆነ በደንብ መግለፅ። ሌሎች ጥንዶችንም በግብዣው ላይ ማምጣት እንደምንችል ነገረውናል። የእኛ የክብር እንግዳ በመሆን ልንጋብዛችሁ እንወዳለን። በተጨማሪም በዝግጅቱ ላይ» የክርስትና እውነታ በአሁኑ አለም ውስጥ በሚል ርዕሰ ሁለት ባልና ሚስት አጭር ንግግር ያቀርባሉ። የምትችሉ ከሆነ ወዲያው አሳውቁን፣ ምክንያቱም ተመልሰን ለአስተናጋጆቻችን ጓደኞቻችንን እንደምናመጣ መንገር እንድንችል።***
3. የሚመጡ ከሆነ፣ ወደ ግብዣው ትወስዳቸው ዘንድ እንድትችል ከእነርሱ ጋር ተነጋገር። (ይሄ በጣም ወሳኝ ነው።)
4. ግብዣው ላይ እንደደረስክ እየተዘዋወርክ ለምትችለው ሰው ሁሉ አስተዋውቃቸው
5. አሁንም መንፈሳዊ ባልሆኑ ርዕሰ ጉዳዩች እንዲጨዋወቱ አበረታታቸው።
6. ስለ ቤተክርስቲያን አንዳንድ እንቅስቃሴዎች መጨዋወትህን አስወግድ።

## የሐሳብ መስጫ ካርድ

ስም:- ________________________________________________

አድራሻ:- ______________________________________________

ከተማ:- _________ ክ/ከተማ ____________ ቀበሌ ______________

አስተያየቶች:- (በአንድ ወይም በሁለት ዐ.ነገሮች ከዝግጅቱ ምን እንደተማርክ ተናገር)

- ☐ ዛሬ በመፀለይ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወቴ ጋብዣለሁ
- ☐ ከኢየሱስ ክርስቶሰ ጋር እንዴት የግል ግንኙነት ማድረግ እንደምችል ለመማር እፈልጋለሁ።
- ☐ የቤት ቤተክርስቲያናችሁን መካፈል እፈልጋለሁ።


## የሐሳብ መስጫ ካርድ

ስም:- ________________________________________________

አድራሻ:- ______________________________________________

ከተማ:- _________ ክ/ከተማ ____________ ቀበሌ ______________

አስተያየቶች:- (በአንድ ወይም በሁለት ዐ.ነገሮች ከዝግጅቱ ምን እንደተማርክ ተናገር)

- ☐ ዛሬ በመፀለይ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወቴ ጋብዣለሁ
- ☐ ከኢየሱስ ክርስቶሰ ጋር እንዴት የግል ግንኙነት ማድረግ እንደምችል ለመማር እፈልጋለሁ።
- ☐ የቤት ቤተክርስቲያናችሁን መካፈል እፈልጋለሁ።

## የሐሳብ መስጫ ካርድ

ስም:- ________________________________________________

አድራሻ:- ______________________________________________

ከተማ:- _________ ክ/ከተማ ____________ ቀበሌ ______________

አስተያየቶች:- (በአንድ ወይም በሁለት ዐ.ነገሮች ከዝግጅቱ ምን እንደተማርክ ተናገር)

- ☐ ዛሬ በመፀለይ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወቴ ጋብዣለሁ
- ☐ ከኢየሱስ ክርስቶሰ ጋር እንዴት የግል ግንኙነት ማድረግ እንደምችል ለመማር እፈልጋለሁ።
- ☐ የቤት ቤተክርስቲያናችሁን መካፈል እፈልጋለሁ።

## የሐሳብ መስጫ ካርድ

ስም:- ________________________________________________

አድራሻ:- ______________________________________________

ከተማ:- _________ ክ/ከተማ ____________ ቀበሌ ______________

አስተያየቶች:- (በአንድ ወይም በሁለት ዐ.ነገሮች ከዝግጅቱ ምን እንደተማርክ ተናገር)

- ☐ ዛሬ በመፀለይ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ህይወቴ ጋብዣለሁ
- ☐ ከኢየሱስ ክርስቶሰ ጋር እንዴት የግል ግንኙነት ማድረግ እንደምችል ለመማር እፈልጋለሁ።
- ☐ የቤት ቤተክርስቲያናችሁን መካፈል እፈልጋለሁ።

# የሚመሩ መሪዎች

## ክፍል ስድስት

እያንዳንዱን ነጥብ ከአሰልጣኝህና ከሌሎች መሪዎች ጋር ከተወያየህ በኋላ በዚህ ምልክት (✓) ምልክት አድርግባቸው፡፡

**የመሪነት ቡድኑን ከማገናኘትህ በፊት ቅድመዝግጅት፡-**

☐ 1. **የመሪነት መሰረት** የተሰኘውን ክፍል አንብብ ለመወያየት ተዘጋጅ

☐ 2. **«በግንኙነት ውስጥ ያለ አዲስ አንድ መሆን»** የተሰኙውን ክፍል አጥና፡፡ ከመሪነት ቡድኑ ጋር ለመከፋፈልና ለመወያየት ተዘጋጅ፡፡

☐ 3. **«እንዴት በቡድንህ ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ ለማግኘት እንደምትችል»** የተሰኘውንና **«የአገልግሎት ኃላፊነት»** የተሰኘውን ክፍል አጥና፡፡ ከመሪነት ቡድኑ ጋር ለመከፋፈልና ለመወያየት ተዘጋጅ፡፡

☐ 4. ከዚህ በታች ያለውን ሪፖርት አጠናቅ

**ከመሪነት ቡድንህ ጋር በመሆን የሚከናወን፡፡**

☐ 5. እያንዳንዳችሁ የራሳችሁን ምስጋና እና የፀሎት ጥያቄዎችን አካፍሉ፡፡ ቡድናችሁ ስለሚያስፈልገው ነገር ተነጋገሩ፡፡

☐ 6. ከተወያየህ በኋላ ከላይ ከ1-4 ያሉትን ነጥቦች በዚህ (✓) ምልክት አድርግ

**በዚህ ወር የህይወት ቡድንህን ትመራ ዘንድ ስልጣን መስጠት**

☐ 7. የህይወት ቡድናችን በክርስቶስ የሆነውን አንድነት ያሳያል? አንድነታችንን ለማሻሻል ምን ማድረግ

ያስፈልገናል?________________________________________________
________________________________________________________

ከእኔ ጋር ፀልይ ________________________________________________

☐ 8. ከ14ቱ መርህዎች የቡድንህን ጥረት ታሻሽል ዘንድ ለመተግበር የምትፈለገው የቱ ነው? ምን ለማድረግ አቅደሃል?

____________________________________________________
________________________________________________ አቅጃለሁ፡፡

**ስለ ሕይወት ቡድንህ ዘገባ**

☐ 9. ______________ ሰዎች በመደበኛነት ይሳተፋሉ፡፡
☐ 10. ______________ አዳዲስ ተሳታፊዎች በዚህ ባሰለፍነው ወር ተካፍለዋል፡፡

ስም ________________________________________________________________

አድራሻ ______________________________________________________________

☐ 11. በአንድ ለአንድ ስልጠና ላይ ያሉ

ዳይናሚክ መሰረታዊን ____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
ዳይናሚክ ደቀመዝሙር ማድረግን ____________________________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
ዳይናሚክ ማካፈልን ____________________ ____________________ን ያሰለጥናል
____________________ ____________________ን ያሰለጥናል

☐ 12. _________ ሰዎች በዚህ ወር በቡድናችን ውስጥ ባሉ ሰዎች አማካኝነት ክርስቶስን እንደ አዳኛቸው አድርገው ተቀብለዋል፡፡

**ፀሎትና መዝጊያ**

☐ 13. እርስ በእርስና ለቡድን አባላቶቻችሁ ፀልዩ፡፡

☐ 14. አሰልጣኝ ለመሆን ካቀድህ፣ ወደ ክፍል አንድ **የአሸናፊዎች ቡድን - የአሰልጣኞች ስልጠና እና የመርጃ ፅሁፎች** አልፈህ ሂድ፡፡

☐ 15 ለመጀመሪያው የአሸናፊዎች ቡድን ክፍለግዜ ቀን________________ ሰዓት ____________________ ቦታ ____________________ መድብ

# የመሪነት መሰረት

መሪዎች በሌሎች ህይወት ተፅዕኖ ከማምጣታቸው በፊት፣ በባህሪይ እድገታቸው ላይ ሆን ብለው የሚያተኩሩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

**የመሪው አስተሳሰብ**

- አገልግሎት ሰዎች ናቸው፡፡ (ሁልግዜ አገልግሎት ከግንኙነት ይወጣል)
- ግባችን የተለወጡ ህይወቶችን ማየት ነው፡፡
- የሰዎችን ህይወት ለመለወጥ በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንደግፋለን፡፡

**የመሪው ዋና ተግባር**

- በተለወጠ ህይወት ራዕይ መጣልና ቀስ በቀስ ማስተማር
- በሰዎቹ ፊት ስለተለወጠ ህይወት የሚያወራ ታሪክ መናገር
- በግል የአገልግሎት ችሎታ ማስታጠቅ
- በማለማመድ ተተኪን ማፍራት
- መሪዎችን ማሰልጠን

**የመሪው ባህሪይ**

- ከእግዚአብሔር የሆነውን ተልዕኮ ይፈፅም ዘንድ ስጦታውን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እያሰራ እግዚአብሔርን ለማክበር መፈለግ፡፡
- በሌሎች ውስጥ ለተልዕኮ ጥልቅ ስሜት እንዲኖራቸው ማቀጣጠልና ፀጋቸውን እየተለማመዱ ተልዕኮውን እንዲፈፅሙ መርዳት፡፡
- ኃላፊነትን መቀበል፣ ስልጣንን መውሰድና ለተጠያቂነትን ዝግጁ መሆን

**ከመሪዎች የሚጠበቁ**

**ታማኝነት**፡- ለእርስ በእርስ፣ ለቡድኑ ና ለስልጣን
**መጓጓት**፡- ሌሎች በህይወትና በአገልግሎታቸው የተሳካላቸው እንዲሆኑ ለመርዳት
**አመለካከት**፡- ለመማር ፈቃደኛ የሆነ፣ ቅን፣ የሚያግዝ
**የተሰጠ**፡- ለክርስቶስ ፣ ለእርስ በእርስ ፣ ለአገልግሎት
**አበረታች**፡- በሌሎች አማኞች ውስጥ ያሉ ህልሞችን
**እውነተኝነት**፡- እውነተኛና በቀላሉ ለመገኘት ፍቃደኛነትን ማሳየት

## *መሪነት = ተፅዕኖ ማድረግ*

# አዲስ አንድነት በግንኙነት

ብዙ ጊዜ በማማከር ክፍለ ግዜ ይህንን ትሰማለህ፣ **«ከእንግዲህ በኋላ እርሱን/ እርሷን ልወዳት አልችልም!»** ብዙ ጊዜ እንዲህ እላቸዋለሁ **«ከእንግዲህ በኋላስ?»** በመቀጠልም **«ከዚህ በፊት ትዋደዱ ነበር?»** ብዬ እጠይቃለሁ፤ብዙ ግዜ መልሳቸው **"አዎን"** የሚል ይሆናል። እንዴት ነው እርስ በእርስ የሚዋደዱ ሰዎች አንዱ ላንዱ የጥላቻ ስሜት እስኪሰማቸው ድረስ ቅር ወደሚሰኙበት ሁኔታ የሚገቡት? በአንድ ጠዋት ልክ ከአልጋቸው እንደተነሱ ሁሉም ነገር የተቀያየረ ይመስልሃል? አይደለም። በማንኛውም ግንኙነት ውስጥ በአንድ ግዜ አንድ እርምጃ እየተቀራረብን ልንመጣ እንችላለን ወይም በአንድ ግዜ በአንድ እርምጃ እየተራራቅን ልንመጣ እንችላለን። ይህንን ሁኔታ ደረጃን ከመውጣት ጋር አነፃፅረዋለሁ። እያንዳንዱ ትክክለኛ ውሳኔና ተያይዞ ያለው እርምጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እርስ በእርስ ወደምትደናነቁበት ከፍታ ይወስዳችኋል። ባንፃሩ፣ እያንዳንዱ ትክክለኛ ያልሆነ ዉሳኔና እርምጃ ወደታበች ያወርድሃል። ወደታች መውርድ ማለት ለግንኙነት የሚሆን ምንም እስከማይቀር ድረስ እራስን መወሰንና መገደብ ነው። አስታውስ «ነገርግን እኔ ሳልሆን ክርስቶስ» የሚለውን፤ መጠየቅ ያለበህ ትክክለኛው ጥያቄ «ክርስቶስ ሌላውን ሰው ይወደዋል?» ማለት ነው። በእርግጥ ይወዳል! አሁን ወደ እውነተኛው ነገር ውስጥ እየገባን ነው። ክርስቶስ በእኔ አልፎ የጠላሁትን ሰው እንድወድ መፍቀድ እችላለሁ?

## በክርስቶስ ሙሉ የሆነ አንድነት ይገኛል

ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝህ አድርገህ ከተቀበልክ፣ 100% በክርስቶስ ውስጥ ነህ። ነገር ግን በክርስቶስ ውስጥ በመሆን ካላረጋገጥክ በክርስቶስ ውስጥ ለመሆን ብርቱ ትግል ታደርጋለህ። ተግባርህ የመረዳትህ ውጤት ነው። በዛ የመረዳትህ አቅጣጫ ክርስቶስን ወደ መምሰሉ ይወስደኛል ብለህ ተስፋ ወዳረከው የክርስቶስ እውቀት ፍቃዱና መንገዱ ምርጫ ታደርጋለህ። ይህ ጥሩ ስሜት ሊሰጥ ይችላል ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ስህተት ነው። ይሄ ህግን በመጠበቅ ፅድቅን ለማግኘት መፈለግ ነው።
1ኛ ቆሮንቶስ 1÷30 እንዲህ ይላል፣ «በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤» በቆላስያስ 2÷10 ላይ ደግሞ፣ በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል ይላል። እምነት እግዚአብሔር ያለውን ሁሉ ይቀበላል። የሚከተለውን ልብ በል።

**በክርስቶስ፡-**

1. ዳግመኛ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ። 1 ጴጥሮስ 1÷23
2. ከኃጢያቴ ሁሉ ይቅር ተብያለሁ። ኤፌሶን 1÷7 ፣ ዕብራዊያን 9÷14፡ ቈላስያስ 1÷14፣ 1ዮሐንስ 1÷9፣ 2÷12
3. አዲስ ፍጠረት ነኝ። 2ቆሮንቶስ 5÷17
4. የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነኝ። 1 ቆሮንቶስ 6÷19
5. ከህግ እርግማን የተዋጀሁ ነኝ። 1 ጴጥሮስ 1÷18-19፣ ገላትያ 3÷13
6. የተባረኩሁ ነኝ። ዘዳግም 28÷1-4፣ ገላትያ 3÷9
7. ቅዱስ ነኝ። ሮሜ 1÷7፣ 1 ቆሮንቶስ 1÷2፣ ፊሊጵስዩስ 1÷1
8. በፊቱ ቅዱስና ያለነቀፋ ሆኜአለሁ። 1 ጴጥሮስ 1÷16፣ ኤፌሶን 1÷4
9. ተመርጬአለሁ። ቈላስያስ 3÷12፡ ሮሜ 8÷33
10. እስከመጨረሻው ፀንቼ ቆሜአለሁ። 1 ቆሮንቶስ 1÷8
11. በክርስቶስ ኢየሱስ ደም በኩል ቀርቤአለሁ። ኤፌሶን 2÷13
12. ከክርስቶስ ጋር ወራሽ ሆኜአለሁ። ሮሜ 8÷17
13. ተስፋ ሆኖ በተሰጠው መንፈስ ታትሜያለሁ። ኤፌሶን 1÷13

14.ከእርሱ የተነሳ በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን በቅቻለሁ።1 ቆሮንቶስ 1÷30
15.በሚወደው አንድ ልጁ በኩል ተቀባይነት አግኝቻለሁ። ኤፌሶን 1÷6
16.በእርሱ ሙሉ ሆኜአለሁ። ቈላስያስ 2÷10
17.ከእግዚአብሔር ጋር ታርቄአለሁ። 2 ቆሮንቶስ 5÷18
18.በእግዚአብሔር ተጠርቼአለሁ። 2 ጢሞቴዎስ 1÷9
19.የፍጥረቱ በኩር ሆኜአለሁ። ያዕቆብ 1÷18
20.ተመርጫለሁ። 1 ተስሎንቄ 1÷4፣ ኤፌሶን 1÷4፣ 1ጴጥሮስ 2÷9
21.በኢየሱስ ቁስል ተፈውሻለሁ። 1 ጴጥሮስ 2÷24፣ ኢሳያስ 53÷5
22.በእግዚአብሔር ተወድጃለሁ። ሮሜ 1÷7፡ 1 ተስሎንቄ 1÷4
23.ህይወቴ ከክርስቶስ ጋር በእግዜአብሔር ዘነድ ተሰውሯል። ቈላስያስ 3÷3

**በክርስቶስ፡-**

24.ርስትን አግኝቼአለሁ። ኤፌሶን 1÷11
25.በአንድ መንፈስ ወደአብ መግባትን አግኝቼአለሁ። ኤፌሶን 2÷18

በየጊዜው እነዚህን እውነቶች ለቡድን አባላትህ ልታሳስባቸውና የተቋረጠ ግንኙነታቸው እንዲጠገን ልትረዳቸው ይገባሃል። **አንድ ናቸው** ስለሆነም የሆኑትን እንዲሆኑ እርዳቸው።

# በቡድንህ ውስጥ ጥሩ ተሳትፎ ስለማምጣት

በተመረጠ ዕቅድና በብዙ ፀሎት ስራህን ብትሰራም እንኳ ያልጠበካቸው ክስተቶችና ብልሽቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። አንድ ማስታወስ ያለብህ ዋና ነገር፣ በሁሉም ሁኔታዎች አዎንታዊ አመለካከት ሊኖርህና እግዚአብሔር በርከት ባሉ ሰዎች ህይወት ውስጥ እየሰራ ባለው ሁልጊዜ ልትደሰት ይገባሃል።በእያንዳንዱ አጋጣሚ እንደ ሁኔታው ለመዘጋጀትና ለማድረግ በትእግስት ራስህን ስጥ። ኃዋርያው ጳውሎስ ምናልባት አንተ እራስህን ሊሰማህ ያሉትን ስሜቶች ምናልባት አልፎባቸዋል፤ ነገር ግን ከራሱ ደቀመዛሙርት ህይወት እግዚአብሔርን ማመን በቀላሉ የተማረና፣ በነዚህም የህይወት ተሞክሮዎች እግዚአብሔር በራሱ ህይወት ውስጥ እያሳደገ ስላላቸው ጥራት ያላቸው ነገሮች እግዚአብሔርን ያመሰግን ነበር። ስለዚህ አይቀሬ በሆኑት ብልሽቶች/መስተጓጎሎች/ አትጨነቅ። በቀላሉ የበለጠ ውጤታማ ለመሆን እንደሚረዱ ተግዳሮቶች አድርገህ ውሰዳቸው። የቡድንህ አባላት ከትምህርትህ እንደሚማሩ ሁሉ ከምላሾችህም የበለጠ ይማራሉ። (ሮሜ 5÷3-5ን አንብብ)

1. ***አንድ ሰው ብቻ የመጣ ቢሆንስ?*** *ያንን ሰው የበለጠ እንድታውቀው ከጌታ እንደተሰጠህ ልዩ ጊዜ አድርገህ ቁጠረው። ያልመጡትን ሰዎች እንዳትወቅስ ተጠንቀቅ። ከዛ ሰው ጋር ለማጥናት፣ ለመካፈል፣ ለማቀድና ለመፀለይ ጊዜውን ተጠቀምበት።*

2. **ሰዎቹ ለ 45 ደቂቃ ያረፈዱ ቢሆንስ?** በፍጥነት አጫርና ግልፅ ባለ መልኩ ምን እያደረጋችሁ እንደነበረ መንገርና እንዲቀላቀሉ መፍቀድ።

3. ***ሰዎች ከትምህርቱ ጋር አግባብነት የሌላቸውን ነገሮች ቢናገሩስ?*** በሌላ አገላለፅ ከርዕሰ ጉዳዩ ውጪ ቢሆኑስ? *ሁልግዜ ግልፅ ሁን። እንደዚህ በማለት ወደ ርዕሱ ልትመልሰው ትችላለህ፣* ***«እኛ በሌላ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እንዳለን አስባለሁ። ከጊዜ አንፃር ለምንድን ነው ወደ*** *______የመነጋገሪያ ርዕስ የማንመለሰው?» ምናልባት ርዕሱ ሁሉም እንዲያውቁት አስፈላጊ ሆኖ መወያየት ከፈሉጉ ወይም ሁሉም የጓጉለት ነገር ከሆነ የርዕሱን ማስታወሻ አድርግበትና ሌላ ግዜ ለማጥናት ጊዜው ላይ ተስማሙ።*

4. ***አንድ ሰው ብዙ የሚያወራ ከሆነስ?*** *ይህንን ለመመለስ ቀላል አይደለም፣ ነገር ግን ችግሩ መሪው በቡድኑ ውስጥ ያለውን ሌላውን ሰው፣* ***«ወንድሜ አንተስ በዚህ ጉዳይ ምን ታስባለህ?»*** *ቢል ችግሩ በቁጥጥር ስር ሊውል ይችላል። ለዚህም ለመመለስ በቂ መተማመን ያለውን አንድ ሰው ምረጥ። ችግር የሚደጋገም ከሆነ መሪው በግሉ ከእርሱ/በእርሷ ጋር መነጋገርና እርሱ/እርሷ የተናገረችው ጥሩ እንደሆነ ማስረዳት፣ ነገር ግን ሌሎች እራሳቸውን ለመግለፅ ነፃ መሆን የሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንዳሉ መንገር። ምናልባትም በውይይቱ ውስጥ ዝም በማለት እንዲተባበሩህ ልታሳስባቸው ትችላለህ።*

5. **አንዱ የተሳሳተ መልስ ቢሰጥስ?** *ሰውየውን እንዳታሳፍረው ተጠንቀቅ። ነገር ግን እንዲህ ማለት፣* ***«ይህ የሚያስደስት ነገር ነው። አንድ ሰው በዚህ ላይ የሚለው ነገር ይኖራል? ወይም አንድ ጥቅስ ወይም የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍል ይህንን ሐሳብ የሚደግፍ ይኖራል?»***

6. **የአንዱ ጥያቄ ወይም መልስ አግባብ ባይሆንስ?** በፍፁም ልንደነግጥ አይገባም ወይም ባልተጠበቁ ወይም ክህደት በሚመስሉ መልሶች እንኳ ቢሆን። የኛ ቀዳሚ አላማ ያልዳኑት ጓደኞቻችንና ጐረቤቶቻችንን ከእግዜአብሔር ቃልና ከፍቅሩ ጋር ማስተዋወቅ እንደሆነ ማስታወስ ይኖርብናል፤ ብዙውን ጊዜ ብቸኞችና ግራ የተጋቡ ናቸው። እናም የመፅሀፍ ቅዱስን ዋና መልዕክ በማሳየት ልንረዳቸው ያስፈልጋል። (1 ቆሮንቶስ 15÷3-5) እስቲ የእግዚአብሔርን ያለቅድመ ሁኔታ የሆነ ፍቅርና ተቀባይነት ማግኘት በእኛ ውስጥ ይዩ።

7. **አንድ ሰው ሁልግዜ ስለራሱና ስለችግሮቹ ቢናገርስ?** *መሪው* ከሰውየው *ጋር* በግሉ ቢነጋገር ምናልባት በቂ ሊሆን ይችላል። ሰውየውን ለችግሮቹ እንደመልስ ወደ እግዜአብሔር ቃል መምራት በጣም የሚረዳ ነው። እርሱ ወይም እርሷ የማማከር አገልግሎትን ከሚሰጥ መጋቢ ተጨማሪ እርዳታ ሳያስፈልገው አይቀርም። ምናልባት እርሱ/እርሷ ክርስቶስን እንደግል አዳኝና ጌታ ያልተቀበሉ ከመሆናቸው ባሻገር፣ በራሳቸው ጥረትና በሌሎች ሰዎች እየታመኑ ሊሆን ይችላል።

8. **አንድ ሰው ከኃሜት የተነሳ ስሌላ ግለሰብ ወይም ስለቤተክርስቲያን አሉታዊ አመለካከት ቢኖረውስ?** ፅኑ ፍላጐት፣ በመሪው በኩል ያለ ጉጉነትና አዎንታዊ አመለካከት በቡድኑ ይያዛል። ጥሩ አመለካከት የሌለው ግለሰብ በፍጥነት ሊታረም ያስፈልገዋል፤ ነገር ግን በግል መሆን አለበት፤ በሌላው ግለሰብ ላይ መልካም ያልሆነ ነገር ካለው፣ መሪው መፀለይ እንደሚያስፈልገውና የልቡንም አመለካከት እንዲያስተካክል ማሳሰብ ይኖርበታል። (ማቴዎስ 7÷35) ከዚህ በኋላ፣ በግለሰቡ ሕይወት እስካሁን ችግር እንዳለ ከገመተ ከዛ ሰው ጋር በጉዳዩ ላይ በቀጥታ ለመወያየት መሄድ ይኖርበታል። (ማቴዎስ 18÷15-17)

9. **አንድ ሰው አከራካሪ /አወዛጋቢ/ ርዕስ ጉዳይ ቢያመጣስ?** አወዛጋቢ ጉዳዩችን ለመመከት አተፍራ፣ ነገር ግን ቡድንህ የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻ ባለስልጣን መሆኑን መገንዘካቸውን አረጋግጥ። ለመልሶች የመፅሀፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተመልከት። መሪው በቡድኑ ውስጥ ያለን አንድን ሰው ጥናት አድርጐ በሚቀጥለው ሣምንት ተዘጋጅቶ እንዲመጣ ምናልባት ሊመድብ ይችላል። ነገር ግን እርሱም ራሱ ከዚሁ ርዕስ ላይ ጥናት በማድረግና ለመወያየት መዘጋጀቱን እርግጠኛ መሆን አለበት።

10. **አንድ ሰው ከዚህ በፊት ባለው ሳምንት በነበረው ውይይት ከህይወቱ ጋር እንዲያዛምዳቸው የተነገሩ ነጥቦችን ባይተገብራቸውስ?** የመሪው ምሳሌ ወሳኝ ነው። የመሪው የትምህርት አተገባበር መመሪያዎች አጭርና ግልፅ ሊሆኑና እያንዳንዱ በዚህ ሳምንት በስራ ላይ የሚውለው የትምህርቱን አላማ የሚያሳካ መሆን ይኖርበታል።

11. **አንድ ሰው ከጉባኤው ጋር ያልተዋወቀ ከሆነና በውይይቱ ውስጥ ለመግባት አይንአፍር ቢሆንስ?** ሰውየውን ካለበት ሁኔታ ለማውጣት፤እንደዚህ የመሳሰሉ ነገሮችን ማለት ***«ወንድማችን በአ.አ ለተወሰነ ግዜ ኖረዋል፣ ምናልባት እዚያ ያየውን _____ነገር ቢነግረንስ?»***

12. **አንድ ሰው በደፈናው ቢናገርስ?** ንግግሩን ግልፅ በማድረግ እንዲህ ብለህ ጠይቅ ***«በዛ ነጥብ ላይ ለየት ያለ ምሳሌ ልትሰጠኝ ትችላለህ? ጠቅለል ያለ ሀሳብህ ጥሩ ነው፡ ነገር ግን ተጨባጨ ይሆንልን ይሆን? አንድ ሌላ ሰው ከዚህ ሀሳብ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ያለው?»***

13. **አንድ ሰው ያልበሰለ ወይም አሉታዊ አመለካከት ቢገልፅስ?** ዘለህ ኃሳቡን ለማስተካከል አትከመርበት፣ ተወያይ ወይም ስበክ፤ይህንን ማንነቱን ምን እንደሚስፍልገው ለማወቅና የአንተን የዕድገት ልምድ ለማካፈል እንደ ጥሩ አጋጣሚ ተመልከተው። ለምሳሌ አንዱ እንዲህ ሊል ይችላል፣« ***ከመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ነገር አላገኘሁም።»***፤እንዲህ በማለት ልትመልስለት ትችላለህ፣***«እኔም እንዲሁ አንድ ሰው እንዴት እንደሚነበብ እስከሚያሳየኝ ድረስ እንዳንተው ነበርኩ...ምናልባት በዚህ መልኩ ብታየው ሊረዳህ ይችላል»***

14. **አንድ ሰው ከአንድ ሰው ጋር እየተቆጣ መከራከር ቢጀምርስ?** እንደዚህ የመሳሰሉ ነገሮችን ማለት፣ ***«በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለቱ ወንድሞቻችን ያላቸውን አስተያየት ሁላችንም እንደምናውቅ አስባለሁ። አሁን ማነው በዚህ ውይይት ውስጥ መግባት የሚፈልግ?»*** በማለት እድሉን ለሌሎች መስጠት።

# የአገልግሎት ኃላፊነት

| አጋጣሚ/ ፍላጐት | የትንሹ ቡድን መሪዎች | አስልጣኝ/ሽማግሌ ሰራተኞች | ሌሎች |
|---|---|---|---|
| **ሞት (በቤተሰብ ውስጥ)** | እርዳታ፣ፀሎት ምግብ፣ ሌላ እገዛ | ማወቅ፣ ስልክ መደወል፣ የሀዘን መግለጫ ካርዶች መላክ፣ መጐብኘት | ቡድኑን መርዳት |
| **ልደት** | በሆስፒታል መጐብኘት ለህፃኑ የሚሆኑ ነገሮችን መስጠት ወ.ዘ.ተ | ማወቅ፣ እንኳን ደስ አለህ ለማለት ስልክ መደወል | |
| **የገንዘብ ችግር** | ሁኔታዉን መስማት፣ ፀሎት፣ ተግባራዊ እርዳታ | ከአማካሪ ጋር ማገናኘት | |
| **ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ መንቀሳቀስ** | ማገዝ፣ ምግብ ማቅረብ | | |
| **መንፈሳዊ ችግር ወይም እስራት** | የቡድን ድጋፍ፣ ፀሎት፣ ክትትል | ማማከር፣ ከበድ ባሉ ጉዳዩች ውስጥ መግባት፣ የነጻነት 7 ደረጃዎች | ተስማሚ የቡድን ድጋፍ |
| **በሱስ መጠመድ** | የቡድን ድጋፍ | ወደ ተገቢ ቡድን ወይም ድርጅት መምራት | 12 ደረጃ ኘሮግራም፣ ከሱሰኞች ቡድን ነፃ መውጣት |
| **የጋብቻ ችግር** | ማዳመጥ፣ ማካፈል ፀሎት፣ ክትትል | ማማከር፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ጉዳዩን ማስተላለፍ | ለጋብቻ አማካሪዎች ማስተላለፍ |
| **ምረቃ፣ የመታሰቢያ በዓል** | የደስታ መግለጫ ካርድ መላክ፣ አብሮ ማክበር | የእንኳን ደስ ያላችሁ መግለጫ | |
| **በወንጌል የመለወጥ ፍላጐት** | ወንጌሉን ማካፈል፣ ለክትትልና ደቀመዝሙር ተስማሚ ሰው መመደብ | ማወቅ | |
| **ጥምቀት ወይም አባልነት** | የጥምቀት ወይም የአባልነት ትምህርት እንዲከታተሉ ማበረታታት | ለጥምቀትና ለአባልነት ትምህርት በመደበኛ የሆነ ማስታወቂያ ማቅረብ | |
| **በግል ለማደግ / የአገልግሎት ፍላጐት** | ፀጋቸውን መለየት፣ አንድ ለአንድ ደቀመዝሙር ማድረግ፣ ለተተኪ መሪነት መመልመል | ማማከር፣ በመሪነት እንዲያድጉ ማሰልጠን፣ በአገልግሎት ማሰማራት | ቀጣይነት ያለው የመሪነት ስልጠና መስጠት |

## የአሰልጣኝ ቃል መግቢያ ቅፅ

እኔ ______________________ ክርስቶስን እና የዕርሱን ቤተክርስትያን ለማገልገል እራሴን በእግዚአብሔር ፊት እሰጣለሁ። በእኔ ስር ያሉትንና አለምን በፍቅር ለመድረስ የአገልጋይ መሪነትን አገልግሎት ለመስጠት እመኛለሁ።

አድራሻ ____________________________________________

____________________________ ስልክ ቁጥር ________________________

ለቤተክርስቴያናችን እንደ አሰልጣኝ ከተመደብኩ እራሴን ለ፦

______________________ በየቀኑ ለመፀለይ

______________________ በእምነት እንደ መፅሀፍ ቅዱስ መመሪያ ለመኖር

______________________መንፈስ ቅዱስ ህይወቴን እንዲቆጣጠር ልፈቅድ

______________________ ለጌታ አገልግሎት በመደበኛ አስራት ለማውጣት

______________________ ለቤተክረስቲያንና ለመሪዎች ታማኝና የተሰጠ ለመሆን

______________________ የአሰልጣኝ መሪዎች ስብሰባንና ስልጠና በመደበኛ ለመከታተል።

እራሴን ለመስጠት ቃል እገባለሁ

# የምስክር ወረቀት

ይህ የምስክር ወረቀት

ለ፡ ____________________________________________

***የህይወት ቡድን መሪ ስልጠናን***

በሚገባ ስላጠናቀቁ ተሰጥቷቸዋል።

ቀን ______________________